

የእንደቢዩ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን።

# ትንሣኤ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ፍሬ እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

# ማውጫ

## አርእስት

ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእስ አንቀጽ (በውኃ በመጠመቅ ሁለተኛ ወለድን) ........ ፪
የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና ዓላማው ........ ፬
የእንደቢዩ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ........ ፭
የቅዱሳን ክብር ........ ፯
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ ፱
ሥራ ጸሎት ነው ........ ፲፩
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፫
ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ........ ፲፬
ዜና ሊ.ቃውንት ........ ፲፭
ከራሔል እምነት ምን እንማራለን ........ ፲፯
የመጀመሪያው ተአምር ........ ፲፰
ኤጲፋንያ ........ ፳
የዓይደ ወይን ምሳሌነት ........ ፳፩
ወንድምህን እንደራስህ ውደድ ........ ፳፫
በደንቢዶሎ ያለችው ቤተ ክርስቲያንና ልማቱ ........ ፳፬

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ፣

ከጥያቄዬ አስቀድሜ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከዚህም ጋር በማያያዝ ያልገቡኝን ጥያቄዎች ሣቀርብ ላቀርብኳቸው ጥያቄዎች ብቁ መልስን ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ነኝ ።

የማቀርባቸውም ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ· ቅዱስ ያሬድን ዘእምነገደ ጌዴዎን ይላል እንጂ የቅዱስ ያሬድ አባትንና እናትን አይጠራም ስለዚህ የአባቱ ስም ማን ይባላል የእናቱ ስምስ ?

፪ኛ/ የቅዱስ ያሬድ ትውልድ ሀገሩ ውጭ ነው ወይስ ኢትዮጵያዊ?

፫ኛ/ ቅዱስ ያሬድ የነበረው በስንት ዓ·ም ነው?

፬ኛ/ አንዳንድ ሰዎች ቅዱስ ያሬድ ተሠውሮ ነው ያለ እንጂ አልሞተም ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ሙቶ ተቀብሮአል የሚሉ አሉ ታድያእውነተኛውና ትክክለኛው የትኛው ነው?

፭ኛ/ ውዳሴ ማርያምን የደረሰ ቅዱስ ኤፍሬም መሆኑ ይታወቃል አንቀጸ ብርሃንንስ የደረሰ ሊቅ ማን ይባላል?

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን

### መልስ

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን

፩ኛ/ ቅዱስ ያሬድን በትምህርት ያሳደገ የአክሱም ገበዝ የነበረው ጌዴዎን የተባለ የእናቱ ወንድም መሆኑ በተለያዩ ታሪኮች ይገኛል ወላጅ አባቱ ግን አብዩድ ይባላል እናቱም ክርስቲና ትባላለች ።

፪ኛ/ ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ ነው ወይስ የውጭ ሀገር ተወላጅ ነው ስለ ምትለውም ቅዱስ ያሬድ ቅልቅል የሌለበት ንጹሕ ኢትዮጵያዊ ነው የተወለደውና ያደገበትም ትግራይ ክፍለ ሀገር አክሱም አውራጃ ልዩ ስሙ መደባይ ታበር ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ ነው ።

፫ኛ/ በስንት ዓ/ም ነበር ስለምትለውም በ፮ኛው መቶ ዓ/ም በአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት ነው ።

፬ኛ/ ቅዱስ ያሬድ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደባርቅ አውራጃ ሰሜን በተባለው ተራራ እንደተሠወረ ነው የምናምነውና ታሪኩም የሚገልጸው ።

፭ኛ/ አንቀጸ ብርሃንን የደረሰው ራሱ ቅዱስ ያሬድ ነው ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አ·አ·

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታ እያቀረብኩ ያልገቡኝን ነገሮች እንዲያብራሩልኝ መንፈሳዊ ነኮች የሆኑ ጥያቄዎችን አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ በእናታቸው ማኅፀን ጃን ደረባ (ሕጽዋን) ሆነው የተወለዱ አሉ ፣ ፪ኛ ስለመንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ሕጽዋን ያደረጉ አሉ ፫ኛ ሰው የሰለባቸው አሉ ይላል ማቴ·፲፱·፲፪ በዚህ አንጻር በጭካኔ አባለ ዘራቸውን በገዛ እጃቸው ቆርጠው የሚጥሉና የሚመነኩሱ አሉ ይህ ተግባር ተገቢ ነውን? እንደዚህስ የሚያደርጉ ይጸድቃሉ ወይ?

፪ኛ/ ለሞተ ሰው ሙሉ ፍትሐት ማግኘ ፍትሐት ይደረግ ሲባል እሰማለሁ ይህ ነገር በፍትሐ ነገሥት አለወይ?

፫ኛ/ አንድ ቄስ የንስሐ ልጁ ሲሞት የሟቹ ወራሾች ከሰጡት ንብረት በስተቀር ስጦታው አነሰ ተቀነሰ ብሎ ቅሬታ ማሳየት ይገባዋልን ?

፬ኛ/ ስለ ሥዕለት እያሉ በቅዱሳንና በመላእክት ስም በየመንገዱ ቆመውየሚለምኑአሉ፣ናለምኖመስጠት ይሻላል ሠርቶ ከደከሙበት ንብረት መስጠት ይሻላል?

፭ኛ/ የጌታችንና የእመቤታችን ፡ የመላእክትንና የጻድቃንን ሥዕል እየያዙ በየመንገዱ መስቀል በማሳለም ገንዘብ እየሰበሰቡ ማታ ወደመጠጥ ቤት እየሄዱ አብዝተው በመጠጣት እየሰከሩ ካህናትን የሚያሰድቡ አሉ ፣ ይህንን ቤተ ክህነት እንዴት ይመለከተዋል?

ተክሉ ደስታ

### መልስ

አቶ ተክሉ ደስታ ላቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ አጸፋውን በመስጠት ለጥያቄዎችዎ መልስ እንሠጣለን ።

የመጀመሪያው ጥያቄዎ የራሳቸውን አባለዘር በእጃቸው የቆረጡ መናንያን መነኮሳት መኖራቸውን ጠቅሰው ተገቢ መሆኑንና አለመሆኑን ማብራሪያ መልስ እንዲሰጠዎ ጠይቀው በተጨማሪ ይጸድቃሉ ወይ? ሲሉ ጠይቀዋል ።

ጠላትን ድል ለማድረግ ከተፈለገ ፣ የድል መሣሪያን እንደያዙ ነው እንጂ መሣሪያውን ጥሎ ጠላትን ድል ለመንሣት አይቻልም ከሰይጣንም ጋር ተጋድሎ አድርጎ ድል ለማድረግ የሚቻለው አባለ ዘርን ቆርጦ በመጣል ሳይሆን በጾም በጸሎት በስግደት በመ

(ወደ ገጽ ፫ ይዞራል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# በውኃ በመጠመቅ ሁለተኛ ወለደን

ሥጋዊ ደማዊ የሆነ ፍጡር ሁሉ የመባዛትና የመራባት የመታመምና የመሞት ባሕርይ አለው ሥጋውና ደመ ነፍሱ በሞት ከተለያዩ በኋላ እንደሰው የመነሣት ሥልጣን ስለሌለው ሕይወቱ በሞት ያከትማል ፡ ሰው ግን የሁለት ዓለማት ነዋሪ መሆኑን ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን ፡ በሥጋው በምድር ላይ ለተወሰነ ዘመን ኖሮ ከሞተ በኋላ በነፍሱ ለዘለዓለም ይኖራል የኑሮው ሁኔታ የሚወሰነው ደግሞ እንደሥራው ነው የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቆ ትእዛዙን አክብሮ ከኖረ ከሞተ ሥጋ በኋላ የሚኖረው በመንግሥተ ሰማያት ሲሆን በሕይወተ ሥጋ ሳለ መልካም ሥራ ካልሠራ የሚኖረው መከራና ሥቃይ በበዛበት በሲኦል በገሃነም ነው።

በምድርም ሆነ በሰማይ ተደስቶ ለመኖር ሁለት ጊዜያት መወለድ ያስፈልጋል ይኸውም አንደኛው በሥጋ ፡ ሁለተኛው በመንፈስ ነው አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን እግዚአብሔር እንዳይበሉ ያዘዛቸውን የዕንጨት ፍሬ ተደፋፍረው በበሉ ጊዜ ወዲያውኑ ከገነት ወጥተው ወደፈጣሪ ቢያለቅሱ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሙቶ ተነሥቶ እንደሚያድናቸው ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር ። የተሰጣቸው የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በማኅፀነ ድንግል ያለ ዘር ያለሩካቤ ተጸንሶ ተወለደ ፡ ከተወለደ በኋላ አምላክ ነኝና በቶሎ ማደግ አለብኝ አላለም ቀስ በቀስ ጥቂት በጥቂት አደገ በጊዜው በዕብራውያን ልጆች ይደረግ የነበረውን ሕግ ሁሉ ፈጽሟል በስምንት ቀን ቤተ ግዝረት ሲወሰድ በ፵ ቀን ዕጉለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተ መቀደስ ይዘውት ገብተዋል ።

በአንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜያት ሕፃናትን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወስዶ እጅ ማስነሣት የተለመደ ስለነበር ጌታችንም እመቤታችንና ዮሴፍ ሰሎሚ እየወሰዱ እጅ ያሥነሡት ነበር በ፴ ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቆ የማስተማር ተግባሩን ከመቀጠሉ አስቀድሞ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሂዶ ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ጾመ ፡ በጾሙም መጨረሻ ሰይጣን በስስት በትዕቢትና በፍቅረ ንዋይ ተፈታተነው ክርስቶስ ግን አልተሸነፈለትም በስስት የመጣውን በትዕግሥት ፡ በትዕቢት የመጣውን በትሕትና ፡ በፍቅረ ንዋይ የመጣውን በጸሊአ ንዋይ ድል ነሥቶታል ።

ከዚያ በኋላ የማስተማር ተግባሩን ቀጥሏል ፡ በዚያም ዘመን ኒቆዲሞስ የሚባል ሰው ነበር የሕዝብ አለቃና ምሁረ ኦሪት በመሆኑ ቀን ወደ ክርስቶስ ሂዶ ለመማር አልቻለም ምክንያቱም ሕዝቡን በማስተዳደር ጊዜ ሊያገኝ አልቻለምና ነው ፡ ነገር ግን ሌሊት እየሄደ ለመማር ስለፈለገ ሌሊት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እየሄዱ ከሚማሩት ሰዎች ቀደም ብሎ ወደ ጌታችን በመሄድ መምህር ሆይ ከእግዚአብሔር ተልከህ እንደመጣህ እናውቃለን አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት ማንም ሊያደርግ አይችልም አለው ጌታችንም በእውነት እልሃለሁ ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ሲል መለሰለት ኒቆዲሞስ በቁሙ ልደተ ሥጋ ስለመሰለው ሰው ካደገና ከሸመገለ በኋላ ወደ አባቱ አብራክ ተመልሶ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሲል ጠየቀው ጌታችንም በእውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው ፡ ስለዚህ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋችኋል ስላልኩህ አታድንቅ ካለ በኋላ በምሳሌ ሲያስረዳው ነፋስ ወደወደደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከየት እንደሚመጣና ወደትም እንደሚሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው ብሎታል ፡ ዮሐ.፫,፩-፰

የጌታችን ትምህርትና የኒቆዲሞስን ንግግር መሠረት በማድረግ ምሥጢረ ጥምቀት በዚህ ጊዜ እንደተመሠረተ የሚናገሩ ሊቃውንት አሉ ።

ወንድ በ፵ ሴት በ፹ ቀን በተጠመቁ ጊዜ የሥላሴ ልጆች ይሆናሉ ይህንን ታላቅ ምሥጢር የክርስቶስ ተከታዎች የሆን አምነን እንቀበለዋልን ።



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አብም በደመና ሆኖ ይህ የምወደው የምወልደው ለተዋህዶ ለመሥዋዕትነት የመረጥኩት ልጄ ነውና እርሱን ስሙት በማለት መስክሯል ፡ ማቴ.፫.፲፯

ይህ በአንድ በኩል የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያስረዳ ሲሆን በሌላ መንገድ በክርስቶስ አምነው ለሚጠመቁ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያድርባቸው ያስተምራል ፡ በእግዚአብሔር አምነን የተጠመቅን ሁሉ ሁለተኛ ከሥላሴ ተወልደናልና የሥላሴ ልጆች ነን ልጅ ልጅ የሚባለው የወለደውን የአባቱን አሠረ ፍኖት የተከተለ እንደሆነ ነው የአባቱን አሠረ ፍኖት ካልተከተለ ግን ልጅ ተብሎ ሊጠራ አይችልም ።

በዚህ አንፃር እኛም በጥምቀት ከሥላሴ ልጅነትን አንድ ጊዜ አግኝተናል ብለን ከእምነት ርቀን ከበጎ ምግባር ተራቁተን ብንገኝ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤቶች ለመሆን አንበቃም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "የአብርሃም ዘር ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ማለት አይደለም ምክንያቱም እግዚአብሔር አብርሃምን ዘር የሚወጣልህ በይስሐቅ ነው ብሎት ስለነበር ነው ስለዚህ በሥጋ የተወለዱት የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም ነገር ግን ዘር ሆነው የሚቆጠሩት የተስፋው ቃል ልጆች ብቻ ናቸው ብሏል ሮሜ ፱,፯-፱ ከላይ እንደተነገረው በ፵ ቀን በ፹ ቀን ተጠምቀን ከሥላሴ ልጅነትን አግኝተናል እያልን ከሃይማኖትና ከመልካም ምግባር ጽሩአን ሁነን ከመታየት ይልቅ በጥምቀታችን ሳንመካ ሃይማኖታችን አጽንተን ሥነ ምግባራችን አሳምረን እንኑር ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ሳሰሉትም ሥነ ምግባራት ነው ።

አባለ ዘርን መቁረጥ በሲኖዶስ እጅግ በጣም የተወገዘና የተነቀፈ ነው ሲኖዶስ ቀኖና ፳፩ና ፳፱ገጽ ፻፺፩ ላይ በፈቃዱ ተደፋፍሮ አባለ ዘሩን የቆረጠ ሰው ክህነት ያለው ቢሆን ከክህነቱ ይሻር ነፍሰ ገዳይ ነውና ሦስት ዓመት ከምእመናን ተለይቶ በቀኖና ይኑር "ይላል ይጸድቃሉ ወይ? ስላሉት እኛ ሕጉን ጠቅሰን ማስረዳት እንጂ ይጸድቃሉ ወይም ይኮነናሉ ብለን አስተያየት ለመስጠት እንችልም እግዚአብሔር ቢያጸድቅ ማን ይኰንናል ተብሎ ተጽፏልና ።

ሁለተኛ ለሞተ ሰው ሙሉ ፍትሐት ግማሽ ፍትሐት የሚል በፍትሐ ነገሥት አልተጻፈም እኛም አናውቅም ።

በሦስተኛው ጥያቄዎ ላይ የንስሐ አባት ከሚች ንብረት መውሰድ እንደሚገባው ጠቁመው እነሡ ተቀነሰ ማለት ይገባዋልን ብለዋል ፡ ሟቹ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ወዶ ከተናዘዘለት ንብረት በስተቀር የንስሐ አባት መጠየቅም የለበትም ቅሬታም ሊኖረው አይገባም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለንስሐ አባት ይህንን ንብረት ስጡ ተብሎ አልተጻፈምና ።

አራተኛው ጥያቄ ለምኖ ከመዘከርና ከደከሙበት ከመዘከር የትኛው እንደሚበልጥ ጠይቀዋል ፡ ሁሉም ድካምን የሚጠይቅ ነው ሥዕለቱ የሚፈጸመው ተሳዩ ባደረገው ቃል ኪዳን ነው ። ለምኖ እዘከራለሁ ብሎ ተሥሎ እንደሆነ ስለቱ ሲፈጸምለት ለምኖ ሰብስቦ ለተራቡት ቢያበላ ለተጠሙት ቢያጠጣ የሚነቀፍ አይደለም በቅዱስ መጽሐፍም የተጻፈ ነው ለምሳሌ ዮፍታሄ የተባለ አንድ መስፍን ከሥለት የተነሣ የገዛ ልጁን ለእግዚአብሔር ሠውቷል ።

መጽ/መሳ ምዕ ፲፩,፳፱-፵ ይመልከቱ፡ እየለመኑ ገንዘብ ሰብስበው ማታ ማታ አብዝተው ጠጥተው እየሠከሩ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያስነቅፉ ቤተ ክህነት እንዴት ያለ አመለካከት እንዳለው ጠይቀዋል ። ጥያቄው አዲስ ባይሆንም ጥሩ ጥያቄ ነው ። ቤተ ክህነት እንደነዚህ ያሉትን ተሰድበው የሚያሰድቡትን ተዋርደው የሚያዋርዱትን ካህናት መሳዮች ወፈፎች እሺ ቢሉ በምክር እለዝቦ በኮርስ አሠልጥኖ በተገቢው ቦታ መድቦ ራሳቸውን እንዲያውቁና እንዲረዱ እያደረገ ነው ብዙዎችን በሥራ መድቧል የቀሩም ቢኖሩ ወደፊት ይከታተላቸዋል ። በዚህ አጋጣሚ በዚህ አስነዋሪ ተግባር የተሰለፉ ካሉ ወደካህናት ማሠልጠኛ እየመጡ ለመሠልጠን ቢሞክሩ መልካም ኑሮ ለመኖር እንደሚችሉ እናሳስባቸዋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና ዓላማው

ትውልድ ሲያልፍ ትውልድ ይተካል ሥርዓትም ሲያልፍ ሥር ዓት ይተካል፡ሥራግንየሚሠራው ዘመንን ተከትሎ ነው ፤ በቀድሞ ዘመን ከተሠሩት ሥራዎች አል ፈው አልፈው ተደናቂነት ያላ ቸውሥራዎችሲገኙሊሻሻሉየሚገ ባቸውም አሉ ፤ የቤተ ክርስቲያን ተግባርም የሚከናወነው እንደጊ ዜው ነው ፤ የማይሻሻል ፤ የማይቀ ነስ የማይጨመር ፤ ሃይማኖት ነው እንጂ ሥራን በሚያስፈልገው መንገድ እያሻሻሉ መሥራት ያስ መሰግናል እንጂ አያስነቅፍም ።

ልጅ ተወልዶ ለቁም ነገር የሚበ ቃውና እርሱም በተራው አባት ተብሎ የሚጠራው በአንድ ቀንና በሁለት ቀን ዕድሜ አይደለም ቀስ በቀስ ካደገ በኋላ ብዙ ዘመን ቆይቶ ነው ፤ በዚህ አንጻር የሰበካ ጉባኤን አጀማመርና ዕድገት ስን መለከት ለቤተ ክርስቲያናችን ያቀረበው አገልግሎትና የደረሰ በት ደረጃ እጅግ በጣም ከፍ ብሎ እናገኘዋለን ፤ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ዘመኑ ሲቆጠር ፲፯ ዓመት ነው ይህ ዘመን አጭር ነው ባይባልም ብዙ መንፈሳውያን ተግባሮች ተፈጽመዋል ፤ በተጠቀሱት ዘመ ናት ውስጥ ብዙ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት ታድሰዋል ፤ አዳዲ ስም ተሠርተዋል ፤ ሁሉም በጠቅ ላላ ሳይሆኑ ጥቂቶች ካህናትም የወር ደመወዝተኞች ለመሆን በቅተዋል ፤ የገዛ ቤተ ክርስቲያና ቸውን ጥፋትም ሆነ ልማት አሻግ ረው ይመለከቱ የነበሩ ምእመና ንም አሁን ከካህናቱ ጐን በመሰ ለፍ የሚፈለግባቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት በንቃትና በትጋት በማከናወን ላይ ይገኛሉ ።

ወደ ሰንበት ት/ቤት የተመለከ ትን እንደሆነ ደግሞ ዕድሜያ ቸው የሚፈቅድላቸው ታዳጊ ሕፃ ናት ከሥጋዊ ትምህርት ጋር በዕረ ፍት ጊዜያቸው መንፈሳዊ ትምህ ርትን እየተማሩ በሥጋ ብቻ ሳይ ሆን በመንፈስም እንዲጐለምሱ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጥረት እያደረገ ነው ፤ ቤተ ክርስቲያና ችን በአሁኑ ጊዜ ከምታደርጋ ቸው እንቅስቃሴዎች ሌላው ክፍል የልማት ተግባር ነው ።

ልማት ሲባል መሬትን አርሶ ቆፍሮ ዘር ዘርቶ ማብቀል አትክል ትን ተክሎ ማጽደቅ ብቻ ሳይሆን የተማሩ ሊቃውንት እንዲያስተ ምሩ ያልተማሩ እንዲማሩ ልብስ ቀለብ እንዲያገኙ ማድረግም ፤ ከልማት ዘርፎች አንዱ ነው ፤ እንዲሁም ጋዜጦችና መጽሔቶች በብዛት እየታተሙ ለምእመናን እንዲዳረሱ ለማድረግ የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት የአንድ ካህን ደመወዝ በየወሩ እንዲከ ፍሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ያለ ምንም ችግር መክፈላቸውም ቤተ ክርስ ቲያናችን ከሚያስመሰግኗት ተግ ባራት ታላቁ ቁም ነገር ነው ።



ቅዱስነታቸው የሰበካ መ/ጉባኤን ሲመሩ

ለማስረጃ ያህል አንዳንዱን መጥቀሳችን ነው እንጂ በሰበካ ጉባኤ አማካይነት የተፈጸሙት መንፈሳውያን ተግባራት እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም ።

በየአህጉረ ስብከቱ ተመድበው የሚሠሩ ሊቃነ ጳጳሳትና ሥራ አስ ኪያጆቻቸው ሊቃነ ካህናት በዓ መት አንድ ጊዜ በመንበረ ፓት ርያርክ ስብከተ ውንጌል አዳራሽ እየተሰበሰቡ ይወያያሉ ሪፖር ትም ያቀርባሉ ። ስለሥራቸውም በመነጋገር የጠመመው እንዲ ቃና የጐደለው እንዲሞላ ፤ የተዛ ባው እንዲስተካከል የሰነፉት በር ትተው እንዲሠሩ ፤ በርትተው የሠሩት በበለጠ እንዲሠሩ ብልጫ ላሳዩ የሽልማት ስጦታ ይደረጋል በ፲፱፻፸፪ ዓ·ም· ከጥቅምት ፯–፲፩ ቀን ከቀረቡት ሪፖርቶች መካከል ከፍተኛው የሥራ ውጤትን አስመ ዝግበው የተሸለሙ፡—

<u>በአንደኛ ደረጃ</u>

ሀ· ምሥራቅ ሸዋ
ለ· ምዕራብ ጐጃም
ሐ· ሰሜን ሸዋ

<u>በሁለተኛ ደረጃ</u>

ሀ· ሰሜን ጎንደር
ለ· ኢሉባቦር
ሐ· ሰሜን ኦሞ

<u>በሦስተኛ ደረጃ</u>

ሀ· ጎጃም መተከል
ለ· ደቡብ ኦሞ
ሐ· ሲዳሞ ቦረና ናቸው ።

እንዲሁም በለንደን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ኃላፊ ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴና የዚሁ ቤተ ክርስቲ ያን አገልጋይ ቄስ ተክለ ማርያም የተዘጋጀላቸውን ልዩ ሽልማት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳትዘኢትዮጵያእጅ ተቀብለዋል።

ሽልማቱ በበለጠ ለማነቃቃት የተሰጠ ነው እንጂ የቀሩት አህ ጉረ ስብከት አልሠሩም ለማለት አይደለም አቅማቸው በፈቀደላ ቸው መጠን ሁሉም ሩጠዋል ደክ መዋል ፤ ለሩጫ የተሰለፈው ሯጭ ሁሉ ለመቅደም ስለማይችል ትንሽ ብልጫ ያገኙት ሽልማቱን አግኝ ተዋል ሽልማት በሥራ ለቀደመ ነውና ለሚቀጥለው ዓመት ሽልማ ቱን ለመውሰድ ከዛሬ ጀምሮ ጠን ክሮ መሥራት ያስፈልጋል።

የሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ በዚህ ብቻ የማይወሰን ምን ጊዜም የማያቋርጥ ነው ለቤተ ክር ስቲያናችንም ከዚህ የበለጠ ዓቢይ ተግባር ስለሌላት የሰበካ ጉባኤ ሥም ሪት በሚደረግበት ጊዜ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራውን እያቆየ የመ ምሪያ ኃላፊዎች ሳይቀሩ በሥራው



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መመሪያ ሲሰጡ

እንዲሠማሩ ያደርጋል ። ምእመና ኑም ሆኑ ካህናቱ ጥቅሙን በሚ ገባ በመገንዘባቸው ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቃለለ ፤ ሥራው እየሠመረ በመሄድ ላይ ይገኛል በመንበረ ፓትርያርክ የሚደረ ገው አጠቃላይ (ሰበካ) መ/ጉባኤ ከተጀመረ ፰ኛ ዓመቱ ነው ከቀረ በውም ሪፖርት ለመረዳት እንደ ተቻለው ከዓመት ወደ ዓመት የሚ ታየው ዕድገት እጅግ የሚያስደስ ትና የሚያስመካ ነው ፤ ቤተ ክርስ ቲያናችን አሁን በያዘችው ጐዳና ከተራመደች ራሷን ችላ ሌላውን የምትረዳበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ክቡር ዳዊት ለእግዚአብሔር ስፍራ ለያዕቆብም አምላክ ቦታ እስካገኝ ድረስ በእውነት ወደ ቤቴ እንኳን አልገባም ፤ ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም ፤ ለዓይኖቼም መኝታ ለሽፋሽፍቶ ቼም እንቅልፍ ለጉንጮቼም እረ ፍትን አልሰጥም ፤ ብሎ እንደተና ገረው መዝ ፩—፴፩ ሰበካ ጉባኤ ተጠናክሮ ቤተ ክርስቲያናችን ከመረዳት ወደ መርዳት ደረጃ



www.ethiopianorthodox.org

እስከምትሸጋገር ድረስ ካህናትና ምእመናን ደክመን ሰለቸን ሳይሉ የመሥራት ግዴታ አለባቸው ።

በታላቁ ጉባኤ ማጠቃለያ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ "ሥራው እጅግ አድካሚና ብርታትንና ጥንቃቄን ይጠይቃል የወይኑ ባለቤት ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ለሁሉም እንደ ሥራው ዋጋውን ይሰጠዋልና ሳትሰንፉ ደክመን ሰለቸን ሳትሉ ለቤተ ክርስቲያናችሁ፣ ለሀገራችሁ፣ ለወገናችሁ፡ ጠንክራችሁ ሥሩ" በማለት መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተው ጉባኤው በቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ተፈጽሟል ።

ከቅዱስነታቸው በተሰጠው መንፈሳዊ መመሪያ መሠረት የቃለ ዓዋዲውን ፈር ሳይለቁ ጠንክሮ በመሥራት ልቆ ለመገኘት ከዛሬ ጀምሮ ሁሉም ለሥራ ታጥቆ መሰለፍ ይኖርበታል፡ የሰበካ ጉባዔ ዓላማም ጠንክሮ ሠርቶ ቤተ ክርስቲያንን ራሷን ለማስቻልና የዝቅተኛ ደረጃን ይዞ የሚገኘውን የካህናት ኑሮ ለማሻሻል ነውና ።

# የእንደቢዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ታድሶ ታቦቱ ሲገባ የተደረገ ንግግር

ከብፁዕ አቡነ አብርሃም

"ብፁዕ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር አምላኩ

"እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ ምስጉን ነው ፤ ለርስቱ የመረጠውም የተመሰገነ ነው" አምላኩ እግዚአብሔር የሆነ ሕዝብ ከምድር ወገን (አሕዛብ) ሁሉ እናንተን አወቅሁ ወደድሁ ተብሎ በአምላኩ ቃል የተመሰገነ ነው አሞ. ፫.ቁ ፪" በጎቹን አውቃለሁ በጎቹም ያውቁኛል በፈጣሪው ዘንድ ታዋቂነቱን ያተርፋል በመሠረቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፍጥረቱን ለሥራ ከማሰለፉ በፊት ምድርንና በምድር ላይ ያሉትን አዝርዕትን አትክልቶችን በማዘጋጀት ሠርቶ ማሳያ ጣቢያ ከፈተ። ቀጥሎም እንስሳትን በየወገኑና በያይነቱ ፈጥሮ ካደራጀ በኋላ ሰው በተለይ እንጀራህን በፊትህ ወዝ ብላ (ዘፍ. ፫ ቁ. ፲፰) የሚል መመሪያ ስለተሠጠው የሰው ልጅ ደክሞ ወዙንና ላቡን አንጠፍጥፎ ሕይወቱን እንዲመራ ምድራዊ ኑሮውን እንዲገፋ አድርጎታል ። በመሆኑም "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው ዮሐ. ፲፬. ቁ. ፳፩" ሲል ጌታ መስክሮለታል። እንዲህ በመሆኑም በሥራው ውጤት ወገኑን ሲረዳና ሲጠቅም ይታያል ።



ቅዱስነታቸው በሥራ ብልጫ ላሳዩ ሽልማት ሲሰጡ

ከዚህም የተነሣ በዚህ አካባቢ ያላችሁት ክርስቲያኖች ወይም የእንደቢዮ መድኃኔ ዓለም ተወላጆች ከጉረቤትና ከማንኛውም ድርጅት ርዳታ ሳትጠይቁ ምክራችሁንና ዕውቀታችሁን ገንዘባችሁንና ጉልበታችሁን አስተባብራችሁ በግል ጥረታችሁ ይችን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ከመጣል እስከ መጨረሻ ጉልላትና መርገፍ ሠርታችሁ በዛሬው ቀን ለመድኃኔ ዓለም በማበርከታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ።

ለኛ ሲል ሕይወቱን ለሞት አካሉን ለመሥዋዕትነት አሳልፎ ከሰጠልን የሕይወትና በረከት ሊጋሥ ከሆነው መድኃኔ ዓለም የተትረፈረፈ ጸጋና በረከት ለማግኘት መልካም አጋጣሚ ስለሆነላችሁ አሁንም ደግሜ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ ። እንግዲህ ለማየት ዓይንን የሚማርክ ሁኔታ ባሸበረቃችኋት በዚህች ቤተ ክርስቲያን የውጭ ሥነ ገጽታዋን ብቻ ለመመልከት ሳይሆን ወደ ውሥጥ ገብላችሁ በመቁረብ ሥጋና ደሙን በመቀበል ተጠቀሙበት ይህን ያደረጋችሁ ሥጋውና ደሙን የተቀበላችሁ እንደሆነ ድካማችሁና



ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ

ጥረታችሁ ሁሉ ተጀምሮ በእግዚአብሔር ፊት በክብር መዝገብ ተመዝግቦ ይቆያችኋል ከተመዘገበም ዘንድ ቅንጣት ያህል ሳይጎድልባችሁ ፍጹሙን ክብር ለመረከብ አመች ይሆንላችኋል ። ስለዚህ ይች ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ እንደታደሰች ለልብስ ገላን እንደሚያጥቡለት ሁሉ እናንተ ወንዶችም ሴቶችም ሁላችሁ በንስሐ ታጥባችሁና ታድሳችሁ ሥጋውን ደሙን በመቀበል ቅዱሳን ሁኑ ብሎአልና "ዘሌዋ. ም. ፲፱ ቁ. ፪" ያመናችሁበትና የተማጠናችሁበት መድኃኔ ዓለም የጻድቃን ትውልድ ትባረካለች መዝ ፩፻፲፩ ቁ. ፪" ባለው መሠረት ከራሳችሁ ጀምሮ ይባርክ እግዚአብሔር ይባረክ ላዕሌክሙ ወላእለ ውሉድክሙ" እናንተን ባርኮ ትውልዳችሁን ዘራችሁን ይዞታችሁን ይባርክላችሁ በነፍስ በሥጋም ያክብራችሁ ።

ልጆቻችሁም ከእናንተ በኋላ በእግራችሁ ተተክተው ፡ ምሳሌነታችሁን ወርሰው አርዓያነታችሁን ተከትለው ለሀገር የሚቆረቆሩ ለወገን የሚያስቡ ቤተ ክርስቲያንን እንደናንተ የሚንከባከቡ ያድርግላችሁ። በጠቅላላውም ጸጋውና ረድኤቱ በሁላችሁ ላይ አድሮ ይኑር አሜን።

## የቅዱሳን ክብር

(ካለፈው የቀጠለ)

ከሊቀ ሥልጣናት ሀ/ማርያም ወርቅነህ

ቅዱስ ተብሎ ጽላት ከተቀረጸለት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንም በስሙ ከታነፀለት ቅድስናውን የሚገልጥ መልክ ይደርስለታል ። የሕይወት ታሪኩን የሚገልጥ ገድል ይጻፍለታል። በየጊዜው በሕይወቱም ጊዜ ቢሆን ከዐረፈም በኋላ ቢሆን የሠራው ተአምር ሁሉ ይጻፍለታል ። ከዚህ በኋላ ጻድቁን በጻድቁ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ። ባለው መሠረት የአማላጅነት ቃል ኪዳን እንዳለው ተደርጐ ልመናና ስእለት አስተብቁዖት ይደረግለታል (ማቴ. ፲. ፵፩) ።

ቅዱሳንን የቀደሳቸው እርሱ አምላክ እድመሆኑ የእነርሱን ምልጃ የነርሱንም ልመና እግዚአብሔር በበለጠ እንደሚሰማ ይታመናል ለዚህም አስረጅ አብርሃምን ኢዮብን እንመልከት ፡ ማለት በደለኞች በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከሚጸልዩ ይልቅ አብርሃምን ኢዮብን እንዲጸልዩላቸው እግዚአብሔር አዝዞ እናገኛለን (ዘፍ · ፲፱ · ፯—፰ ፡ ኢዮብ ፵፪ · ፯ — ፰) ስለዚህ እኛም አሁን ጸልዩ ለነ ፡ አስተምሩ ለነ በማለት እንድንጸልይ ቤተ ክርስቲያን ታዛለች።

ቅዱሳን እውነተኞች ሆነው በእውነትም ጸንተው በመላ ሕይወታችውን በተጋድሎ በማሳለፋቸው እውነተኞች የአምላክ ባለሟሎች እንደሆኑ ይታመንባቸዋል ፡ ስለዚህ በነርሱም አማካይነት ምልጃ ማድረግ ጸሎቱ በቶሎ ተሰሚነትን ያገኛል የሚል አስተያየት አለ ። ከዚህም ጋር ይኸን ቅዱስ የቀደስከ አምላክ እኔንም ቀድሰኝ በማለት በጸድቅ ስም ምልጃ ይደረጋል ።

## ቅዱሳን እንደአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አመለካከት

ቅዱሳን የውጭ አገሮችም ብሔራዊያንም ቢሆኑ ገድላቸው ተጽፎላቸው በዓመት ፩ ጊዜ መታሰቢያቸውም እየተከበረ ከ፩ኛው ምእት ጀምሮ እስከ ፲፬ኛው ምእት ዓመት ደርሶ ነበር። ይኸም የአንዲቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ሆኖ በሁሉም ዘንድ ጸንቶ ነበር ። ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ግን በ፲፭ኛው ምእት ዓመት እንደ ነገሡ መንፈሳዊ ስሜት የነበራቸው ሰው በመሆናቸው የቅዱሳን የሕይወት ታሪክ በሰፊው የተነገረ፡ በዓላቸውም የተከበረ እንዲሆን ሕዝቡ ይኸን ወደ መስማት፡ ይኸንም ወደ መከተል ያዘነብላል፤ በዚህን ጊዜ የጣዖት አምልኮ





www.ethiopianorthodox.org

ትና ከንቱ ወይም ባዕድ አምልኮት ይቀራል ፤ የእግዚአብሔር ስም ይቀደሳል የሚል አስተያየትን አመጡ ።

ከእርሳቸው ትንሽ ቀደም ባሉት ነገሥታት አምልኮተ እግዚአብሔር ቀዝቀዝ ከማለቱ የተነሣ በየቦታው ባዕድ አምልኮ ተስፋፍቶ እንደነበር ይገመታል እርሳቸውም እንደነገሡ ይኸው በመቀጠሉ ።

፩ኛ/ ባዕድ አምልኮ እንዲጠፋ አምልኮተ አግዚአብሔር እንዲስፋፋ

፪ኛ/ ባዕድ አምልኮት ወደሚደረግበት ቦታ ሰው ሁሉ እንዳይሄድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመሄጃ ምክንያት ለመስጠት ቅዱሳን በየወሩ በተለያዩ ዕለታት እንዲከበሩ እንዲታሰቡ ፤ በዚያም ጊዜ ዜና ገድላቸው እንዲነበብ እንዲተረጐም አስደረጉ ።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ቅዱስ በየወሩ በተወሰነው ዕለት ሲታሰብ ይገኛል ። የዓመት በዓል ተብሎ በስንክሳሩ እንደተጻፈ ሁሉም በተለያየ ጊዜ ይከበራል በጸሎት ይታሰባል ፤ ግን በየወሩ ቅዱስ ሁሉ እየታሰበ በዓሉ እየተከበረ እንዲውል በዚያን ጊዜ የዚያው አጥቢያ ሕዝብ ብቻ በየቤተክርስቲያኑ እየተሰበሰበ እንዲውል ፤ በዐሉን እንዲያከብር መታሰቢያውን እንዲያደርግ ተወስኗል ። ከሌላው ዓለም ክርስቲያናዊ ሥርዓት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የተለየች የሚያደርጋትም ይኸና ይኸን የመሳሰሉ ሥርዓቶች ናቸው ። ይኸም ውሳኔ እስካሁን እንደ ዶክትሪን ውሳኔ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ተጠብቆና ተከብሮ ይገኛል ፤ ምክንያቱም ክርስቲያኑን ሕዝብ በአንድ ጊዜ ለማግኘትና ለማስተማር አመች ሆኖ ተገኝቷልና ።

ይኸው ሥርዓት በዓሉን ለማክበር ሕጋዊ ግዴታ ከመሆኑ ጋር ለማኅበራዊ ግንኙነት ለመወያያ ቦታና ጊዜ አመች ሆኖ በመገኘቱ ከፍተኛ ጥቅምን ሰጥቶ ይገኛል ። በእያንዳንዱ ቅዱስ ወርኃዊ መታሰቢያ የአጥቢያው ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ የሀገሩን ችግር በሰፊው ተወያይቶ ፤ ለችግሩ መፍትሔ ሰጥቶ የእምነቱን ሥርዓት አክብሮ መልክም ሰጥቶ የክርስትና አባልነቱን ማኅበርተኛነቱን አረጋግጦ ይሄዳል ። ይኸ ትውፊት በመሆኑ ለአሁኑ ጊዜ ክርስቲያናዊ ሥርዓት ብቻ እንጂ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሁሉ የሚያቅፍ ሥርዓት አይደለም እየተባለ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንጂ ብሔራዊ ወይም ሕዝባዊ ሥርዓት አይደለም እየተባለ በመጣል ላይ ይገኛል ግን ብዙ የእምነትና የታማኝነት ምልክት በሕዝቡ ላይ እንዲኖር ያደርግ የነበረው ይኸን የመሳሰለው ሥርዓት ሲቀር ሌላም መተኪያ የሌለው ከመሆኑ ጋር የሚነገረው አዲስ ሥርዓት ከልምዱ ጋር የማይገነዛዘብ በመሆኑ ማኅበራዊ ኑሮ በሁሉም ችግርን ፈጥሮ ይገኛል ።

## ቅዱሳን በአሁኑ ዘመን

ከ፲፮ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን ቅድስና የመስጠት ቅዱስ የማለት ትውፊት ተቋርጧል ፤ ለምን እንደሆነ ግን ምክንያቱ ግልጥ አይደለም ። እንደ ጥንቱ አይብዙ እንጂ የቅድስና ምልክት የሚታይባቸው አባቶች በአንዳንድ ገዳም አሁንም መታየታቸው አልቀረም ግን ዜናቸው ስለማይነገር የሚታዩት የቅድስና ምልክቶች ሁሉ እንዲሁ ተደፍነው ይቀራሉ ።

እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ በቅዱስ ቃሉ መሠረትነት አስቀድመው ቅዱሳን የተባሉትን የሚክስ የሚወቅስ አስተያየት በየጊዜው በመሰንዘር ላይ ይገኛል ፤ ስለዚህ አሁን የቤተ ክርስቲያኗ ውጊያ ይኸን የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ለማስተባበል ነው ።

ቀደም ሲል ቅዱሳን ተብለው ተከብረው ቤተ ክርስቲያን በስማቸው ታንፃላቸው የነበሩ ሁሉ የቅድስና ምልክቶቻቸው ባለማቋረጥ አሁንም ይታያሉ ።

እነርሱም ፦

ሀ/ የቅዱሳን አጽማቸው በአረፈበት አካባቢ የበሽተኞች ፈውስ በብዛት ይገኛል ።

ለ/ የቅዱሳን አጽማቸው በአረፈበት አካባቢ ብርሃን በመታየት ፤ ድምፅ በማሰማት ላይ ይገኛል ።

ሐ/ የቅዱሳን አጽማቸው በአረፈበት አካባቢ ራእይ በመታየትና ሌላ ይኸን የመሰለ የተለያየ ምልክት መታየቱ እንደ ቀጠለ ነው ።

አንዳንድ እምነተ ቢሶችም በአሁኑ ጊዜ ታመው በነዚህ አማካይነት ሲፈወሱ ራእይ በማየታቸው ድምፅ በመስማታቸው ወደ ሃይማኖት እየገቡና ኑዛዜ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። አሁንም ራሱን ብቻ የሚወደው ከራሱም ጋር ብቻ የሚነጋገረው ትውልድ ወደ ቅድስና ሕይወት መለስ እንዲል የቅዱሳንንም ሕይወት እንዲመለከት ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን የቅዱ



# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ካለፈው የቀጠለ

ከመ/ሉሌ መልአኩ

በገዳማቱ ክልል ውስጥ የመነኰሳቱ መኖሪያዎች ፤ የጸሎት ቤቶች ፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ፤ የዕቃና የእህል ማስቀመጫ መጋዝኖች ፤ የምግብ መመገቢያ ቤቶች ፤ ሆስፒታሎች ፤ ወፍጮ ቤቶች ዳቦ ቤቶች ፤ የምግብ ማዘጋጃ ማዕድ ቤቶች ፤ የአልባሳትና የቤተ ክርስቲያን ማገልገያ ዕቃዎች ማስቀመጫ ዕቃ ቤቶች ፤ ሱቆች ወዘተ ይገኙ ነበር ።

ሳንን ዜና ሕይወታቸውን በግዕዝም በአማርኛም እያዘጋጀች በማደል ላይ ትገኛለች ።

ይሁን እንጂ ነቢዩ ዳዊት "ጣዕሙ ወታዕምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር" ብሎ እንደ ተናገረው ማንኛውንም ነገር ለማፍቀርም ሆነ ለመጥላት መቅመስ ጣዕሙን ማወቅ አስፈላጊ ነው (መዝ· ፴፬ · ፰) ። አሁንም ወደ ቅድስና ሕይወት ለመመለስ የቅዱሳንን ሕይወት አስቀድሞ መመልከት ቅዱሳንንም መቅመስ አለበት ። ምንም ዘመኑ የሳይንስ ዘመን ቢሆንም ሣይንስ ቅድስናን የሚቃወም አይደለም ፤ ስለዚህ ሣይንሱንና የቤተ ክርስቲያኑን ትውፊት ለማገናኘት የቤተ ክርስቲያንን ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል። የእግዚአብሔር መገለጫ የሆኑ ቅዱሳን አሁንም ተአምራት ከማድረግ ስለማያቋርጡ የቅዱሳን ክብር አሁንም ይቀጥላል።

ከገዳሙ ውጭም የመቃብር ቦታዎች ፤ የውሃ ጉድጓዶች የአትክልትና የእርሻ ቦታዎች ወዘተ ይገኙ ነበር ።

ለምንና የሄዱ መነኩሳት ጠባይ በሚገባ ተጠብቆ እንዲኖር ፤ ኑሮአቸው ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ወዘተ በማድረግ ገዳማቱን የሚያስተዳድሩ አበምኔቶች ከመነኮሳት መካከል እየተመረጡ ያስተዳድሩ ነበር ። መነኩሶቱም በዓመት ሁለት ጊዜ በአጠቃላይ ስብሰባ (ጉባኤ) እያደረጉ ሥርዓት ፤ አስተዳደር ወዘተ ነክ በሆኑና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይወያዩና በገዳማቱ የተከናወኑትን ተግባሮች የሚገልጽ ዓመታዊ ሪፖርትንም ያዳምጡ ነበር ።

በነዚህም ጉባኤዎች የተለያዩ ገምቢ የሆኑ ውሳኔዎች ይተላለፉ ነበር ፤ አዳዲስ አበምኔቶችም ይመረጡ ነበር ፤ በመጨረሻም ሥጋ እንደመልበሳቸው መጠን በመካከላቸው አልፎ አልፎ ግጭት መፈጠሩ ስለማይቀር ከመነኮሳት መካከል የበደሉና የተበደሉ ይቅር ለእግዚአብሔር በመባባል በመካከላቸው የሰላም መንፈስን ካሰፈኑ በኋላ የጉባኤው ፍጻሜ ይሆን ነበር ።

በገዳማቱ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ግብፃውያን መነኮሳት በተጨማሪ ጥቂት ግሪካውያን ፤ ሮማውያን ፤ ቀጰዶቃውያን ፤ ሊብያውያን ፤ ሦርያውያን ፤ ኑብያውያን፤ ኢትዮጵያውያን ወዘተ መነኮሳትም ነበሩ ። ለምሳሌ ቀደም ሲል ግብጽ ውስጥ ጌታውን በማወክ ስላስቸገረ ተባሮ በስርቆት ፤ በዝርፊያና በግድያ ተግባር ተሰማርቶ ኅብረተሰቡን ሲያውክ የነበረው ኢትዮጵያዊው ጋንግ (ወጠምሻ) ሙሴ ጸሊም አስከፊ ተግባሩን እርግፍ አድርጎ በመተው ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሄዶ ከአበመቃርስ እየተማረና የአበምኔትነት ተግባሩን እያከናወነ በብሕትውና ኖረ ። ገዳሙን ሊዘርፉና ሊያጠፉ በሄዱ ዘላኖች ከሰባት መነኮሳት ጋር በሰማዕትነት ስላረፈ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስነት ማዕረግ ሰጥታዋለች ።

በዚህ አኳኋን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባቶች (መነኮሳት) በግብጽ በረሐ በሚገኙ ገዳማት ውስጥ ሥርዓተ ምንኩስናን እራሳቸው ሊማሩና ገዳማትን በየሀገራቸው ሊመሠርቱ ችለዋል ። ብዙ ምእመናንም በዋሻ የሚኖሩ የበቁ ባሕታውያን የሚፈጽሙአቸውን ታምራት አይተው ለማድነቅና በጸሎታቸውም ከአደረባቸው ደዌ ለመፈወስ ወደሚኖሩባቸው ገዳማት (ዋሻዎች) በብዛት ይጐርፉ ነበር ።

በዚሁ የብሕትውና ኑሮ ለመሳተፍ ወደ ገዳማቱ ይሄድ የነበረው ተራው ምእመን ብቻ ሳይሆን ታላላቆች ሰዎች ጭምር ነበሩ ። ለምሳሌ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ከአባ እንጦንስ ዘንድ ለተወሰነ ጊዜ በመቆየት ሥርዓተ ምንኩስናን ተምሯል ። እንዲሁም የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (፫፻፵፯–፬፻፯) ቴያድ ተባለው አባ ጳኩሚስ በመሠረተው ገዳም ውስጥ ከ፫፻፸፫ እስከ



www.ethiopianorthodox.org

፫፻፹፭ ዓ/ም ድረስ በብሕትውና ቆይቷል ። ጀሮምና (፫፻፵፪–፬፻፳) ሩፊኖስ (፫፻፵፭–፬፻፲ ከኢጣልያ ወደ ግብጽ ተጉዘው ከገዳማቱ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በብሕትውና ኖረዋል ። ቅዱስ (ታላቁ) ባስልዮስ ፫፻፴—፫፻፸፱) በግብጽ ገዳማት በብሕትውና ከቆየ በኋላ ወደ ቁስጥንጥንያ ሄዶ በአባ ጳኩሚስ የብሕትውና ሕግ (ሥርዓት) መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ በቢዛንታይን ገዳማትን መሥርቷል ።

ይኸውም በግብጽ ገዳማት ውስጥ ከቆየ በኋላ ከ፫፻፳ ዓ/ም ጀምሮ በትንሿ እስያ (በቢዛንታይን) የምንናገን ኑሮ በመመሥረት ያስፋፋው ታላቁ ባስልዮስ በተለይ የግሪክና የሩሲያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉበትን የገዳማት (የመነኩሳት) መተዳደሪያ ሕግ አዘጋጅቶ አውጥቷል። ይህም ሕግ መነኮሳት በየቀኑ ሊፈጽሟቸው ከሚገቡ አምልኮዎች ፣ የጉልበት ሥራዎች ወዘተ በተጨማሪ የሙት ልጆችን ፣ በበሽታ የሚሠቃዩ ሰዎችን መነኮሳት እንዴት መርዳት እንደሚገባቸው ይገልጻል ።

እንዲሁም ዮሐንስ ካስያን (፫፻፷—፬፻፴፭ በቴቤዩድና በኒትራን በሚገኙት ገዳማት ለሰባት ዓመታት ያህል በብሕትውና ከቆየ በኋላ ወደ ፈረንሳይ (ጎል) ተመልሶ በ፬፻፲፭ ዓ/ም ጉል ውስጥ ማርሴ አጠገብ ሁለት ገዳማትን መሥርቷል ። ቀጥሎም ግብጽ በብሕትውና በቆየበት ወቅት የተመለከተውንና ያጠናውን መሠረት በማድረግ ሁለት የመነኮሳት መተዳደሪያ ሕጎች (ሥርዓተ መነኮሳት) የያዘ መጻሕፍት ጽፏል።

በማሕበራዊ ኑሮ ላይ ተመሥርቶ ጥራት ባለው መልክ ሳይከብድ ወይም ሳይቀል ለሁሉም እንደሚስማማ ሆኖ በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኮሳት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት በማግኘት ብዙዎቹ ገዳማት እየመሠረቱ በዚሁ የመነኮሳት መተዳደሪያ ሕግ ተጠቅመውበታል ። አሁንም በመጠቀም ላይ ናቸው ።

በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኩሳት በተግባር ላይ በዋለበት ሀገር ግብጽ በአምስተኛው መቶ ዘመን በአትሪቢስ ገዳም አበምኔት በአባ ሺኖዳ ተለውጦ በጣም ከባድ የሆነ ሥርዓተ መነኩሳት (የገዳማት መተዳደሪያ ሕግ) ተዘጋጀ ። አባ ሽኖዳ በ፫፻፹፫ ዓ/ም በአጎቱ በአባ ጥጉል በተመሠረተው ነጭ ገዳም (ጸአዳ ገዳም) ገብቶ በብሕትውና ከቆየ በኋላ በ፫፻፹፭ ዓ/ም በአጎቱ እግር በመተካት የዚሁ ገዳም አበምኔት ሆኖ በውስጡ የነበሩ (የሚኖሩ) ቁጥራቸው ወደ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የሚጠጉ ወንድ መነኩሳትና ወደ አንድ ሺህ ስምንት መቶ የሚጠጉ ሴት መነኩሳይያት ያስተዳድር ጀመር ።

በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኩሳት ሰብአዊ መብትን የሚጠብቅና ለዘብ ያለ በመሆኑ በመላው ዓለም ተቀባይነትን ሲያገኝ የአባ ሽኖዳ ሥርዓተ መነኮሳት ግን በጣም ጥብቅና ጭካኔ የተሞላበት ስለነበረ ከግብጽ ውጭ ተቀባይነትን ስላላገኘ ብሔራዊ የገዳማት ሕግ ሆኖ በግብጽ ውስጥ ብቻ ተወስኖ ቀረ ። ለምሳሌ ጥቃቅን ስሕተቶችን የፈጸመ መነኩሴ በምክርና በማግጸ በመታለፍ ፈንታ በአባ ሽኖዳ ሥርዓተ መነኩሳት መሠረት ይገረፍና በጽኑ እሥራት ይማቅቅ ነበር ።

በብሕትውና ለመኖር ወደ ገዳሙ የሚሄዱትንም ከጊዜ በኋላ እንታዘዝም በማለት እንዳያውኩ በገዳሙ መተዳደሪያ ሕግ መሠረት ለመኖር በፈቃደኝነት ወደው የገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የግዴታ ውል በቅድሚያ እንዲፈርሙ ያስገድዷቸው ነበር ።

ሴራፔውም በመባል የታወቀው የአሕዛብ ቤተ መቅደስ በክርስቲያኖች ሲደመሰስና ዝነኛዋ አረማዊት መምህር ሂፖትያ በ፬፻፲፭ ዓ/ም ስትገደል አባ ሽኖዳም በገዳሙ የሚያስተዳድራቸውን መነኩሳት አሰልፈው ወደ ላእላይ ግብጽ በመሄድ ብዙ የጥንት አረማውያን ሐውልቶችንና ቤተ መቅደሶችን አውድሟል ። እንዲሁም አባ ሽኖዳ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስን በመከተል በ፬፻፴፩ ዓ/ም ኤፌሶን ውስጥ በተደረገችዋ በሦስተኛዋ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ ተካፍሎ የንስጥሮስን የኑፋቄ ትምህርት ተቃውሟል ።

በ፬፻፶፩ ዓ/ም በተደረገችው በኬልቄዶን ጉባኤ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የካቶሊክንና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን አውግዛ ከለየች በኋላ በግብጽ ገዳማት ውስጥ የብሕትውና ኑሮ ከዓለምአቀፋዊነት ወደ ብሔራዊነት (ጠባብ ብሔረተኝነት) እየተለወጠ ሄደ ።

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከአምስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ከካቶሊክና ከግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፣ ከ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ደግሞ ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ከተሰነዘሩባት ተጽእኖዎች ፤ እንዲሁም ብዙ ሀገሮችን ግብጽንም ጭምር ወረው ክርስትናን ለማጥፋት በክርስቲያኖች ላይ ከባድ ሥቃይ ከጫኑት እስላሞች መንፈስ ጠንካሮች በሆኑት መነኮሳቶቿ አጽናኝነት በተዋሕዶ እምነታቸው ጸንተው የኖሩትንና አሁንም ያሉትን ምእመናን በማገልገል ላይ ትገኛለች ። ከገዳማቱም አባዛኞቹ ቢወድሙም እስከ ዛሬ ድረስ በምዕራባዊው በረሐማ ቦታ በኒትራን ሸለቆ አራት የሚሆኑ ገዳማት ፤ በምሥራቃዊው በሬሐማ ቦታ ደግሞ በመናኙ በቅዱስ ጳውሊ (ጳውሎስ) ዘእስክንድርያና በአባ እንጦንስ ስም የሚጠሩ ሁለት ገዳማት አሉ ። እንዲሁም በምዕራቡ በረሐማ ክፍል የእመቤታችን ገዳም ይገኛል ። በእነዚህም ገዳማት በትምህርታቸው የገፉ ግብፃውያን መነኮሳት በብሕትውና ይኖራሉ ።

ከሴቶችም ምንኩስናን የጀመረችና የሴት ገዳም በወንድሟ እንዲሠራ ያደረገች የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያም ናት ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ በመጣው መሠረት አሁን በካይሮ አካባቢ አምስት የሚሆኑ የሴት ገዳማት ይገኛሉ ።

በዚህ አኳኋን በአባ እንጦንስና በተከታዮቹ የተመሠረተው የብሕትውና ኑሮ በግብጽና በመላው ዓለም በመካሄድ ለክርስትና መጠናከርና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል ። አሁንም በማድረግ ላይ ነው።

## ሥራ ጸሎት ነው

ጸሎት ሰውንና እግዚአብሔርን ቃል በቃል የሚያነጋግርና የሚያወያይ የሕይወት ስልክ ሲሆን ሥራም ከማንኛውም ክፋት የሚጠብቅና ወድያና ወዲህ የማያሰኝ የሰላም ዘብ ነው ለማለት ይቻላል ።

በአንድነት በታላላቅ ገዳማት የሚኖሩ መነኮሳት በሥራ ፈትነት እጃቸውንና እግራቸውን አጣምረው ዝም ብለው የሚውሉ አይገኙም ሁሉም ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን ይሠራሉ እንጂ በሥራ ፈትነት የሚውል የለም ።

ካልሠሩና ሥራ ፈትተው ከዋሉ ግን ይወቀሳሉ አባ ለከርሱ ተብለውም ከመሰደብ ይደርሳሉ ።

ሥራን መሥራት የሚወዱ መነኮሳት ግን በገዳሙ ያሉትን አካለ ስንኩሎችን ዓይናቸው የፈረጠውን እጅ እግራቸው የተቆረጠውን ስለሚረዱ በምስጋና ላይ ምስጋናን ከማግኘታቸውም በላይ በገዳሙም ያለ አንዳች ሥጋት ሊኖሩ ይችላሉ ።

ከዚህም የተነሣ መነኮሳቱ እንደየችሎታቸውና እንደ እውቀታቸው እየሠሩ እየደከሙ ራሳቸውን በራሳቸው እየረዱ አረጋውያኑንም እየተንከባከቡ ይኖራሉ ። መነኮሳቱ ከአባታቸው ከከአቡነ እንጦንዮስ ተያይዞ በመጣው የሥራ ልምድና የተግባረ እድ ጥበብ አንድ መነኩሴ ሥራውን ፈትቶ የሚውል አይገኝም የሚታረስና የሚቆፈር መሬት ቢያጡም እንኳ ቁጭ ብለው መዋል እንደ እሬት ስለሚመራቸው ሲሠሩና ሲደክሙ መዋልን ይመርጣሉ ።

እንዲህም ማድረጋቸው ያለ ምክንያት አይደለም ታላቅ ቁምነገር ያለው ነው ይኸውም ፩ኛ/ የሥራን ክቡርነት በሚገባ ስለሚያውቁ ፤

፪ኛ/ ሥራ ራሱ ጸሎት መሆኑን ስለ ተገነዘቡ ፤

፫ኛ/ በአጽንአ ሰዓት ተወስነው እንዲኖሩ ነው እንጂ በሌላ አይደለም። አንድ ሰው በሥራ ከተወሰነ ከሐሜት ከቧልትና ፍሬ ከሌለው ወሬ እንዲሁም ከልዩ ሐሳብ ነጻ ሁኖ ሥራውን ሲሠራ ይውላል እንጂ በሥራው ላይ ሌላ ሐሳብ ሊደቀንበት አይችልም የማንኛውንም ሰብአዊ ተፈጥሮ ስም በከንቱ ለማንሳት አይችልም ።

ከዚህ ላይ ነገርን ነገር ያመጣዋል አፈርንም ድግር ያወጣዋል እንደሚባለው ሁሉ ለመግቢያ ያህል ይህንን ጠቀስኩ እንጅ ዋና ፍሬ ነገሩ ሌላ ሥውር ምሥጢር ለመግለጽ ነው።

ይኸውም በኤርትራ ክፍለ ሀገር በአካለ ጉዛይ አውራጃ በሰንአፈ ወረዳ እንዳባ መጣዕ አቡነ ሊባኖስ (ሐም) በተባለው ታላቅ ገዳም አካባቢ ከዚህ በፊት የተለያዩ ቅርሶች የተገኙባትና አስደናቂ የሆኑትን ታሪኮች ተገኝተውበት ታላቅ ስም ያተረፈ ቢሆንም አሁንም በዚሁ ገዳም አንድ አዲስና አስደናቂ ነገር ተገኝቷል ነገሩም ምን እንደሆነ የተገኘውስ ምን ዓይነት እንደሆነ አቶ ብርሃኔ መለስን ጠይቀናቸው እንዲህ ሲሉ ገልጸውልናል ።

በአቡነ ሊባኖስ ገዳም በርከት ያሉ መነኮሳትና የዘጉ ባሕታውያንም ይገኛሉ ታድያ በዚሁ ገዳም የሚኖሩት መነኮሳት ከገዳሙ አካባቢ ያለውን ቦታ እየቆፈሩ ጎመንን ዘርተው ሽንኩርትንም ተክ



www.ethiopianorthodox.org

ለው የሚጠቀሙ ሲሆኑ እንዲሁም እርሻን እያረሱ በመጠኑ ከመጠቀም በቀር ሌላ ረዳት የላቸውም ።

በዚህበአቡነሊባኖስገዳምከሚኖሩት መነኮሳት መካከል አንዱ አባ ተወልደ ብርሃን የተባሉ ባሕታዊ ሥራን ፈትቶ መዋልን ስለማይወዱ ቤተ ክርስቲያኑን ሰፋ አድርጐለማሠራትሐሳብስለነበራቸው የቤተ ክርስቲያኑን ዙርያ በዶማ ሲቆፍሩ ዶማቸው ከእንጨት ላይ እያረፈ በጣም አስቸገራቸውና እሳቸውም የምን የእንጨት ሥር ነው የሚያስቸግረኝ ብሰው አፈሩን በአካፋ አድርገው ገለጥ ገለጥ ቢያደርጉት የተረበረበ ከጥድና ከወይራ የተጠረበ እንጨት ተረብርቦ አገኙት በዚህ ጊዜ ባህታዊው አባ ተውልደ ብርሃን ማን የቀበረው እንጨት ይሆን እያሉ እየተገረሙ አንድ ባንድ እየመዘዙ አንድ ላይ ከመሩትና ከዚህ በታችስ ምን ይኖር ይሆን በማለት እንደገና ወዳታች ቢቆፍሩ እንጨቱ ተረብርቦበት ከነበረው በታች የተጠረቡ ድንጋዮችን አገኙ ድንጋዮችንም አንድ ባንድ እያሉ ቢያነሱአቸው ትልቅና ሰፊ ዋሻ አገኙ ።

ዋሻውንም ቢመለከቱት ከዋሻው ውስጥ ከ፫ በላይ የሚሆኑ አስከሬኖች አንዳንዶቹ በዓጽፍ የተጠቀለሉ ፤ ሌሎችም በደበሎ የተሸፈኑ አንዳንዶቹም ነጭ ጋቢ በሚመስል ልብስ የተከፈኑ በያንዳንዱም አስከሬን አንገት መስቀል ታሥሮ አገኙዋቸው ሲሉ ሰፋ አድርገው አስረድተውናል ።

ከዚህም በማያያዝ አቶ ብርሃኔ ሲያስረዱ ባሕታዊው አባ ተወልደ ብርሃን ያንን በማየታቸው ፈርተውና ደንግጠው ሂደው በገዳሙ ላሉት መነኮሳት ነገሩዋቸው ሲሉ አብራርተው ገልጸውልናል ።

ይህ አስደናቂ ዋሻና ከ፫ በላይ የሚሆኑ አስከሬኖች የተገኙበት ቦታ እንዴት እንደነበረ አቶ ብርሃኔ መለሰ ሲያብራሩ ቦታው ከዚህ በፊት ተቆፍሮ እንደማያውቅና ሣርና ቅጠላቅጠሎች የበቀሉበት የመቃብር ምልክትም እንዳልነበረበት ጨምረው አስረድተዋል ። አቶ ብርሃኔ መለስ ስለ ቦታውም አቀማመጥ ሲገልጡ የተገኘበት ቦታ ዙርያው ገደል ሁኖ አንድ መግቢያ ብቻ አለው ዋሻው የሚገኝበትም ቦታ ከዛላ አንበሳ በስተ ምዕራብ ፲፮ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ያለው ነው ከማለታቸውም ሌላ ዋሻው የተቆፈረውና የታየበትም መች ምን ጊዜ እንደሆነ ሲገልጹ ዋሻው የተገኘው በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ሲሆን እኔ ግን ሂጄ በዓይኔ ያየሁት በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ነው ብለዋል። የተቆፈረው በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ከተቆፈረ እንዴት ሳታመለክቱና ሁኔታውን ሳትገልጡ ቀራችሁ ብለን ላቀረብንላቸውም ጥያቄ አቶ ብርሃኔ ሲገልጡ እኛ ከዚህ በፊት ወድያው እንደ ተቆፈረና ዋሻው እንደተገኘ ለብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ገልጸንላቸው ነበር ብሏል ።

አሁንም ቢሆን ይህ አስገራሚና አስደናቂ ነገር እኛ አይተነው ጠ·ቤተ ክህነት ሳያውቀው እንዴት ይቀራል ማሳወቅ ይኖርብናል በማለት እነሆ እዚህ ድረስ የመጣሁ ከዚሁ የተነሣ ነው ከማለታቸውም በላይ ይህንን ለማመልከት የተገደድኩት ዋና ምክንያት ምናልባት በዚሁ አካባቢ ሌላ ታሪክ ወይም ሌላ ቅርስ የተቀበረ ይኖር ይሆናልና ጠቅላይ ቤተ ክህነት አውቆትና አካባቢውን በባለሞያዎች አስመርምሮ ልዩ ጥበቃ እንደሚደረግለት ለማስታወስ ያህል ነው ሲሉ አብራርተው ገልጸውልናል ።

አስከሬኖቹ የተገኙበት ዋሻና የአቡነ ሊባኖስ ገዳም በኢትዮጵያ ውስጥ ታላላቅና ቀደምትነት አላቸው ከሚባሉት ገዳማት አንዱ ነው ።

እንዲያውም ቀደም ሲል ጻድቁ አቡነ ሊባኖስ ባሁኑ ጊዜ ደብረ ሊባኖስ ተብሎ በሚጠራው ገዳም ከአቡነ ተክለሃይማኖት በፊት በተባሕትዎ ለብዙ ዘመን እንደተቀመጡበት ኋላ ግን ይህ ቦታ ክፍልህ አይደለምና ወደ ሌላ ሂድ ስሙን ግን ባንተ ስም ደብረ ሊባኖስተብሎእንዲጠራአደርግልሃለሁ ብሎ እግዚአብሔር እንደነገራቸውና በዚሁ መሠረት በእግዚአብሐር ቅዱስ ፈቃድ አሁን ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ከሚጠራው ገዳም ተነሥተው ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ሄደው ይህንን አስከሬኖች ተከማችተው የተገኙበትን ገዳም አቅንተው የአንድነትንም ገዳም አቋቁመው እንዳለፉ ታሪክ ያስታውሰናል ።

ስለዚህ እንዲህ ያለውንና የታሪክና የቅርሳቅርስ መዲና የሆነውን ገዳም በባለሞያዎች ተመርምሮ ጥበቃ ቢደረግለት መልካም ነው ። እያልን ጥቆማችንንና በጆሮዎችንን የሰማነውን እንገልጻለን ።

ክንፈርግብ ማርቆስ

**ማ ረ ሚ ያ**

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር ፩፻፴፰ ገጽ ፲፪ ዘአምላኪየ ቅኔ ከመ/ሐዲስ ልሣኑ ተበሃሉ ሕዝብ ወግብረ ትሕትና የሚለው ስሕተት ስለሆነ ተበሃሉ ፍቅር ወግብረ ትሕትና ተብሎ ይነበብ ።



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያናችን ለልማት ተግባር እንግዳ አይደለችም በቁመታቸው እና በዕድሜአቸው ከሁሉ ልቀው የሚታዩ ዛፎች የሚገኙት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነውና መንገደኛ ሰው አብያተ ክርሲቲያናት ያሉበትን የሚያውቀው በዛፎች አማካይነት መሆኑ አይጠረጠርም ።

በተለይ በአሁኑ ዘመን ደኖች ተመንጥረው እንዳልነበሩ በሆኑበት ወቅት ዛፎች ለምልክት ያህል የሚታዩት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው ጥቅማቸውን ባለመረዳትም ሆነ በፍላጐት ብዛት ተመንጥረው የተራቆቱትን ቦታዎች መልሶ ደን ለማልበስ በአሁኑ ጊዜ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በመረባረብ ላይ ይገኛል ቤተ ክርስቲያንም ለዚህ ዓላማ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ ታጥቃ ተነሥታለች ።

ከዚህም የተነሣ በየአድባራቱ በየገዳማቱ የተራቆቱትን መሬቶች ካህናት ችግኝ በማልበስ ላይ ናቸው ፤ በየዓመቱ በሚደረገው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሚቀርበው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እጅግ በጣም የበዙ ችግኞች ተተክለው አንዳንዶች ለአገልግሎት የበቁ የደረሱ መሆናቸው ተገልጿል።

እንዲሁም አትክልቶችና አዝርዕቶች እየተዘሩ እየተተከሉና እየጸደቁ የሚሰጡት ጥቅም ለቤተ ክርስቲያን ማደሻ ለካህናት ኑሮ ማሻሻያ እየረዳ ነው ። በባሕር ዳር የተቋቋመው የዓሣ ማስገሪያ ፕሮጀክት በዚያው አካባቢ የተተከሉት ልዩ ልዩ አትክልቶች በቂ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ ።

በጎጃም ሀ/ስብከት በሚገኙት አውራጃዎች አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚፈጸሙአቸውን የልማት እንቅስቃሴዎች ተዘዋውረን ተመልክተናል በመተከል ችግኒ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተተከሉ ባሕር ዛፎች ግማሾቹ ለአገልግሎት መድረሳቸውን ተመልክተናል ። እንዲሁም በሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር አጠገብ ብዙ የባሕር ዛፍ ችግኞች ተተክለው ጸድቀዋል በዳንግላ አውራጃ በአጉታ ኪዳነ ምሕረትም የተተከለው ባሕር ዛፍ የቤተ ክርስቲያኑን አካባቢ የአንበሳ መዋያ ደን አስመስሎታል ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ስለ ልማት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

ከተመለከትናቸው የአብያተ ክርስተያናት የችግኝ አተካከል ከፍ ያለውንና የላቀውን አሠራር ይዞ ያገኘነው በብቸና አውራጃ የሚገኘው እነከርከር ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው የሚገኘውም ብቸና ከአውራጃው ዋና ከተማ በስተምሥራቅ ከከተማው ዳር ላይ ነው ፤ ደብሩን ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በቅርቡ ደብረ መንክራት ብለው እንደሠየሙት ተነግሮናል ።

በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር አጠገብ የሚገኘው አፈር ለችግኝ ማፍያ እጅግ ተስማሚ በመሆኑ ኅብረተሰቡ እየወሰደ ይጠቀምበታል ፤ በደብሩ ሰበካ ውስጥ የሚኖሩት ምእመናን ብዛታቸው ከአንድሺህ በላይ መሆኑ ታውቋል የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ፹ሺህ ሰማንያሺህ የባሕር ዛፍ ችግኞችን አትክሎ ሁሉም የጸደቁለት መሆናቸውን እየተዘዋወርን ተመልክተናል ።

በይበልጥ የሚያስደንቀው የችግኝ አተካከል ነው ችግኙ የተተከለው ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር በግምት ሁለት መቶ ሜትር ራቅ ብሎ ነው ችግኙ የተተከለበት መሬት ስፋት በግምት ስድስት መቶ (፮መቶ) ሜትር ሲሆን የቤተ ክርስቲያኑን ጥዶች ወደ ውስጥ እየተወ ዙሪያውን ይዞራል ፤ ይህ በስፋቱ ስድስት መቶ ሜትር የሆነው ባሕር ዛፍ ራቅ ብሎ ሲመለከቱት እጅግ በጣም ያስደስታል ፤ ችግኙ ከተተከለ ከስድስት ወራት የማይበልጠው ሲሆን ቁመቱ ከሁለት ሜትር ያላነሠ ሆኖ ይታያል ችግኙ ያለበትን መሬት ለመዞር ፴፭ ደቂቃዎች ወስዶብናል።

ስለዚህ ችግኝ አተካከልና ይዞታ እንዲያስረዱን የወረዳውን ሊቀ ካህናት መሪጌታ መክብብን ጠይቀናቸው ሲያብራሩ ችግኙ ከተተከለ ከ6 ወር አይበልጠውም ነገር ግን እንዲህ ፋፍቶ የሚታየው ከመተከሉ በፊት መሬቱ በበሬ ሳይሆን በሰው ጉልበት ብቻ በሚገባ ተደድቆ ፀሐይ ሲመታው ለብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ በወቀቱ ስለተተከለ ነው ከተተከለም በኋላ እንደምታዩት አጥሩ በሚገባ ታጥሮ ከብትም ሆነ ሰው አያልፍበትም ከዚህ ሌላ አጥሩን ሰብሮ ከብት ሲገባ ወይም ሰው ዘሎ ሲገባ የሚጠብቅና አጥሩንም የሚያጠብቅ በቀንም ሆነ በሌሊት አትክልቱን ከሚጐዳ ነገር የሚን



www.ethiopianorthodox.org

ከባከብ ሰበካ ጉባኤው የቀጠረው ዘበኛ አለና እርሱ በቅርብ ሆኖ አትክልቱን ይንከባከበዋል ብለዋል ።

መሪጌታ መክብብ ማብራሪያቸውን በመቀጠል በዚህ አካባቢ የሚገኘው የገበሬ ማኅበር የምንሠራውን ሥራ ተመልክቶ በመደሰት እንድናለማው የሰጠንን መሬት ጤፍ ዘርተን አጭደን ከምረናል በግምት ከ፴ ኩንታል ያላነሰ ጤፍ እንደምናመርት ተስፋ አለን ብለዋል ። መሪጌታ በዚህ ዓመት ስለሚተከለው ችግኝ ሲናገሩ በዚህ ዓመት ልንተክል ያሰብነው የባሕር ዛፍ ችግኝ ፩መቶሺ በላይ ነው በማለት ለችግኝ መትከያ ቃርሶ የተሰናዳውን ቦታ አስጎብኝተውናል ።

የወረዳው ሊቀ ካህናት መሪጌታ መክብብ በዚህ የልማት ሥራ በመቀጠል በቅርብ ቀን የእንክርክር ቅዱስ ጊዮርጊስ አካባቢን አረንጓዴ እንደምናለብሰው እተማመናለሁ በማለት ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል፡

ይህንን የልማት ተግባር በጽሑፍ ያቀረብነው ቤተ ክርስቲያናችን ለልማት ሥራ ከነበራትና ካላት እንቅስቃሴ ላይ በበለጠ ጨምራ እንድታለማ ለማነቃቃትና ለማሳሰብ ያህል ነው በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን የልማት እንቅስቃሴዋን እያጠናከረች በሰበካ ጉባኤ ምእመናንን እያደራጀች ትገኛለች ። በአንዱ ሀገር የተሰራውንና የሚሠራውን የልማት እንቅስቃሴ በጋዜጣና በመጽሔት እያሳተመች የምታሰራጨው በልማት ተግባር ላይ የተሠማሩ በርትተው እንዲሠሩ ያልተሠማሩ ደግሞ ለልማት አመች የሆኑ ቦታዎችን እየቀየሱ መሥራት እንዲጀምሩ ለማሳሰቢ ነው ። ልማትም ሲባል አንድ ወገን ብቻ አይደለም ችግኝ መትከል ልማት ነው ከብት ማርባት ልማት ነው እህል መዝራት ልማት ነው ሌሎችም የመሳሰሉ አሉ፡ ስለዚህ እንደቦታው አመችነት እያጠኑ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የልማት ተግባር ማቋቋም ተፈላጊ መሆኑን የቤተ ክርስቲያናችን አባላት የሆኑ ሁሉ ሊያውቁት ይገባል።

ሊ·ኅ·ልማኀ ወርቅ በዛብህ

# ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ

የመንፈስ ጥንካሬንና ኃይልን ተላብሰው ዓለምን እንዲያስተምሩ ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ተቀብለው አልጫ የነበረውን ዓለም በትምህርታቸው ለውጠው የአገልግሎት ዘመናቸውን ከመፈጸማቸው አስቀድሞ ለሥራቸው መቃናት ሲሉ እምነትና መንፈስ ቅዱስ የመላበት ሰው እስጢፋኖስንና ከእርሱም ሌላ ስድስት ሰዎችን በመምረጥ በሐዋርያት ፊት አቆሙአቸው ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው ቅዱስ እስጢፋኖስን ግን የስድስቱም የበላይ አድርገው ሊቀ ዲያቆን ብለው ሾሙት የሐ· ሥራ ም· ፮ ቁ ፮ ።

የእግዚአብሐርም ቃል ለሕዝቡ በስፋት እየተሰበከ ስለመጣ በኢየሩሳሌም የደቀመዛሙርቱ ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ ከካህናቱም መካከል ብዙዎቹ ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ እስጢፋኖስም በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ተአምራትን ያደርግ ነበር ።

ቢሆንም "በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እንደሚባለው ሁሉ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ያልለወጡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ቃል ያልተቀበሉ በእምነታቸው ጥርጣሬና ሁከተኛነት ያጠቃቸው ሰዎች ከተለያዩ አህጉር መጥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር ።

ይሁን እንጂ ቅዱስ እስጢፋኖስ "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ" ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማቴ· ወ· ም· ፲—፳፰ የተናገረውን ቃል መመሪያው ያደረገና መንፈስ ቅዱስን የተላበሰ ታላቅ ሐዋርያ ስለነበረ ይናገርበት የነበረውን ጥበብና ተአምራትም ያደርገበት የነበረውን መንፈስ ይቃወሙት ዘንድ አልቻሉም።

ይህም በመሆኑ ቅ·እስጢፋኖስ ስለተነግበት ዓላማ ቁርጥ ሀሳብና ቁርጥ ልብ የነበረው ሐዋርያ በመሆኑ ትምህርቱ ከዕለት ወደ ዕለት አማኞችን በሚስብና በሚመስጥ ሁኔታ ማስተማሩን ቀጠለ ይህ በእንዲህ እንዳለ ትምህርቱ ሰዎችን የመማረክና የሰዎችን ህይወት የመለወጥ ኃይል እንደነበረው የተመለከቱት አይሁድ በምቀኝነት ተነሳስተው የሐሰት ምስክር አቁመው በከተማዋ ሸሞች ከሰሱት ። እርሱም በክስ ቆሞ በነበረበት ወቅት በሸንጉ የተቀመጡት ሁሉ እንደመልአክ ፊት መስሎ ስለታያቸው አተኩረው ይመለከቱት ነበር ።

ሊቀ ካህናቱም "ይህ ነገር እንዲህ ነውን" ሲል የተከሰሰበትን ነገር እንዲያስረዳ ጠየቀው ። እስጢፋኖስም ክፉ አለማድረጉን ቢያውቅም እንኳ ለተጠየቀው ጥያቄ ሳይፈራ በድፍረት እንዲህ ይመልስላቸው ነበር ።

"እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ በማለት የልቡናቸውን መሠሪነት ጆሮአቸውም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ለማወቅ ያልተገረዘ መሆኑን ከነገራቸው በኋላ ቀድሞ አባቶቻችሁ ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል ብለው ነቢያት ሲያስተምሩ ልዩ ልዩ መከራ አፈራረቁባቸው እናንተም የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶቢያስተምራችሁለሞትአሳልፋችሁሰጣችሁትገደላችሁትም እያለ መሰከረባቸው ።

ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቆጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት እስጢፋኖስ ግን ወደሰማይ ተመልክቶ መንፈስ ቅዱስንም ተመልቶ በታላቅ ድምፅ እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ እያለሁ አለ ከነርሱም በተላቅ ድምጽ እየጮሁ ጆሮአቸውን ደፈኑ ወደ እርሱም ሮጡ ከከተማም ውጭ አውጥተው በአንድ ልብ ሆነው ወገሩት እርሱ ግን ጌታ ሆይ ! ነፍሴን ተቀበል አለ አይሁድ ግን ስቃዩን አብዝተው ይብስ ይወግሩት ነበር ።

በዚህ ጊዜ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዓላማ የተከተለው እስጢፋኖስ ስለተቀበለው መከራና ስቃይ እንዲሁም ግፍ ሳይቆረቆር ለጠላቶቹ ተንበርክኮ ምህረትን እንዲያገኙ እንዲህ እያለ ጸለየ ጌታሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጥርባቸው ብሎ በክብር አረፈ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ይላል ማር· ፰·፴፬ ጌታችን እንዳለውም ስለክርስቶስ ስለቅዱስ ቃሉ ነፍሱን አሳልፎ የሚሰጥ በክብር ያርፋል ።

በዚህ ሁኔታ ቅዱስ እስጢፋኖስ በአደባበይ ቆሞ በመስበክና የእምነቱንና የምግባሩን ብርታት በማሳየቱ ክርስቶስን በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ በማየቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳገኘ ማወቅ ይቻላል በእውነቱ በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ጠላቶቹ እያስጨነቁትና እያሰቃዩት ሳለ ለጠላቶቹ ምህረትን እንዲያገኙ መጸለዩ ነው ።

ለምሳሌ በጠላት እጅ ተይዞ የሚሰቃይ ሰው ለጠላቱ ሊጸልይ ይቅርና በምን ዓይነት ዘዴ ሊበቀለው እንደሚችል ሲያወጣና ሲያወርድ እንደሚኖር ለማንም የተሰወረ አይደለም ። ይኸውም ከወዳጅና ከዘመዶቹ እንዲጣላ ፍቅር እንዲያጣ በአጠቃላይም ሕይወቱ የሚጠፋበትን ወይም መንፈሱ የሚታወክበትን መንገድ ሲፈልግ ይታያል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከደቀመዛሙርቱ መካከል ገንዘብ ያኘ የነበረው አስቆርታዊው ይሁዳ የክርስቶስ መልካም ሥራ እንዲነቀፍ ደቀመዛሙርቱ እንዲበተኑ ከማድረጉም ሌላ ዓለም ሰላምን እንዲያገኝ ኃጢአተኞች እንዲድኑ የታቀደው ዕቅድ እንዳይሳካ ጌታችን ለመከራ አሳልፎ እንደሰጠው ከታሪክ እንማራለን ።

ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን እራሱ መከራን ተቀበለ ተጋደለ ። የጀመ ከመከራ ላይ አልጣለም ስለዚህም የክርስቶስን አርአያ በመከተል መከራን ተቀበለ ተጋደል ። የመጀመሪያውም ሰማዕት በመሆን የጽድቅ አክሊልን ተቀዳጀ እምነቱንም ሥርዐቱንም ጠብቆ ለዚህ ታላቅ ክብር በመብቃቱ ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ መዝሙሩን እየዘመሩ ዝክሩን እየዘከሩ በዓሉን ማክበር አለባቸው ።

እንግዲህ የቅዱስ እስጢፋኖስን መልካም አድራጐት ተመልክተናል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የምንገኝ አማኞች ከቂም በቀል ርቀን የምንችል ለወገኖቻችን ማስተማር ማሳወቅ በቅዱስ ቃሉ እንዲታነፁ ማድረግ ሲገባን ፣ የማናውቅ ደግሞ ሥርዓቱንና እምነቱን ጠንቅቀን ማወቅ እንችል ዘንድ ሳንሰለች ዘወትር ቅዱስ ቃሉን እንማር ።

መልአከ ፀሐይ ገ/ሥላሴ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## የሊ.ቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ

## አጭር የሕይወት ታሪክ

በድጓ መምህርነታቸው የታወቁት ሊ.ቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ መቄት ውስጥ ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባታቸው ከአለቃ ውሂብ ስንደቁ ከእናታቸው ከወይዘሮ ሀጥሬ ወልደ ገብርኤል በ፲፰፻፹፪ ዓ/ም ጥር ፲፰ ቀን ተወለዱ። በተወለዱ በ፬ ዓመታቸው በተወለዱባት ደብር ከአባ በየነ ፊደል ቆጥረው በ፯ ዓመታቸው ዳዊትና ንባብ የቃል ትምህርት ዜማ ተማሩ ከዚያም ከመሪጌታ ሥርጥ ወርቅ ጾመ ድጓና ቅዳሴ ተምረው የዲቁና ማዕርግ ከአቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል።

ከዚህ በኋላ ወደዞር አምባ አቡነ አረጋዊ ሔደው ከአለቃ ሀብተ ማርያም ዝማሬ መዋሥዕት በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ከዚያም ወደደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም ሄደው ከመምህር ገብረ ወልድ ዘንድ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ።

ሊ.ቀ መዘም[...]ን መንግሥቱ የተማርኩት ምንያ ይበቃኛል ሳይሉ በዚሁ አውራጃ የጥጃ ማርያምና ውቅሮ ጊዮርጊስ በድጓ መምህርነት ከታወቁት ሊ.ቅ ከመሪጌታ እጅጉ ድጓ በሚገባ ተምረው እንደፈጸሙ ወደቤተልሔም ሔደው ከአለቃ [...]ርሻ ዘንድ ድጓ አድርሰው በድጓ መምህርነት አስመስክረው ወደትውልድ ሀገራቸው ወደገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተመልሰው በሥርዓቱ ተክሊልና በክህነት አግብተው ትዳር መሥርተው ከ፲፱፻፲፭ ዓ/ም ጀምረው ድጓ ዘርግተው ያስተምሩ ጀመር። በተጨማሪም በትርፍ ጊዜአቸው ቅዳሴ ከአባ ናሁ ሠናይ ዘንድ አጥንተው የቅስና ማዕረግ ከአቡነ ማቴዎስ ዘንድ ተቀብለዋል ።

ሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ ድጓ አስተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያስረከቡአ



ሊ.ቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ እኒህ ነበሩ

ቸው ደቀ መዛሙርት እጅግ ብዙ ናቸው ከብዙዎቹ መካከል ዛሬ በማስተማር ላይ የሚገኙት ፦

በላስታ መሪጌታ ሐረገ ወይንና መሪጌታ ሰሎሞን ጸጋዬ ፡ መሪጌታ ወረደ ቃል ፡

በዋድላ ደላንታ አለቃ ስጦታውና መምህር መልአኩ መሪጌታ ገብረ ጻድቅ ገላየ ፡

በየጁ አለቃ መዘምርና መሪጌታ ብርሃኑ ፡

በሸዋ መሪጌታ ገብረ ኢየሱስና መምህር ትእዛዙ ዘገየ ይባላሉ ። በድጓ መምህርነት ወንበር ዘርግተው በትግራይ ክፍለ ሀገርም ጥቂት ዘመን ያስተምሩ ስለነበር መሪጌታ ገብረ መድኅንና መሪጌታ መንክር የሚባሉ መምህራን ለድጓ መምህርነት አብቅተዋል ።

ሊ.ቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ ቀን ድጓ በማስተማርና ማኅሌት በመቆም በገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፶፰ ዓመታት አገልግለዋል ።

በተጨማሪም ቅዳሴ በመቀደስ ሰዓታት በመቆም ለምእመናን ሃይማኖትንና ምግባርን በማስተማር ከፍተኛ የሆነ ቁም ነገርን ፈጽመዋል ።

የገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አስተዳዳሪዎች ከነበሩት ከመምህር ስይፈ ሥላሴ ከመምህር ቀጸላ ስይፉ አሁን ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ዘንድ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ያዳምጡና ይሰሙ ስለነበር ሁለቱም መምህራን በጣም ይወዷቸውና ያከብሯቸው ነበር ።

ሊ.ቁሊ.ቀመዘምራንመንግሥቱ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ብራና አውጥተው ቀለም በጥብጠው ቁም ጽሕፈት ያውቁ ስለነበር ብዙ የብራና መጻሕፍቶችን ጽፈው ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት አበርክተዋል ። የራሳቸውንም የዜማ መጽሐፍቶች ለገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ሰጥተዋል ።

ሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ ከደጃች አያሌው ብሩ ቀሚስ ከንጉሥ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ካባ ከቀድሞው ንጉሠ ነገሥት ካባና ቀሚስ የብር መቋሚያና ጸናጽል ተሸልመዋል ።

ሊቀ መዘምራን መንግሥቱ በቤተ ክህነትም ሆነ በቤተ መንግሥት ዝናቸው የታወቀ በጣም ተወዳጅነት የነበራቸው ትዝታቸው ምን ጊዜም የማይረሳ አቋም የነበራቸው ነበሩ ።

ሊ.ቁ ስማቸውን የሚያስታውሱ ፬ ወንዶች ፭ ሴቶች በድምሩ ፱ ልጆችን ወልደዋል ። እንደበታቸው ከጸሎት ሳይለዩ ጥቂት ቀናት ታመው በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም መጋቢት ሁለት ቀን በተወለዱ በዘጠና ስምንት ዓመታቸው ማስተማር በጀመሩ በ፷፭ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በታላቅ ሥነ ሥርዓት በዚሁ በተወለዱበትና በደከሙበት በገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

ተምሮ አውቆ ያልተማሩትን አስተምሮ ያላወቁትን አሳውቆ ለተተኪ ትውልድ መልካም አርዓያነትን ትቶ እንደሊ.ቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብ ማለፍ ከእግዚ. አብሔር ታላቅ ክብርን ያሰጣል። ሞት ሥጋን ለለበሰ ሁሉ የማይቀር ዕዳ ነው ግን እግዚአብሔር በሰጠው ዕድሜ ተምሮ አስተምሮ እንደሊ.ቀ መዘምራን በዕርግና ማረፍ መታደል ነው ።

የታሪኩአቅራቢ.አባገ/መስቀል ተስፋዬ

ዘገተ ማርያም

# የሴቶች ዓምድ

## ከራሔል እምነት ምን እንማራለን?

ስሟ የተጠቀሰው ሴት የሶር ያው የላባ ልጅ ስትሆን የአባታችን የያዕቆብ ሚስት ናት በሕጻንነቷ ወራት ከወላጆቿ ዘንድ የመልካም አስተዳደግ ሥነ ሥርዓት እየተፈጸመላት ስለአደገች በቤተ ሰቧም ሆነ በቅርብ ዘመዶቿ በኩል ጥሩ ታዛዥነትን ከማበርከት የተቆጠበችበት ጊዜ አልነበረም ።

በሌላ በኩል ደግሞ በውበት ብቻ ሳይሆን መልካም ጠባይን ተሟልቶ የተሠጣትና ዘመኑም እንደሚፈቅደው የቤት ባልትና አጠናቃ የምታውቅ ባለሙያ ስለነበረች ሚስት ትሆነው ዘንድ ለጋብቻ ያዕቆብ አባቷን ጠየቀ አባትየውም ለሰባት ዓመት ያህል ደጅ ከስጠናው በኋላ ጋብቻውን ፈቀደለትና ሁለቱ ተጋብተው በሰላም ይኖሩ ጀመር ።

ምንም እንኳን ራሔል ከላይ ለተጠቀሱት ነገሮች ብቁ ሆና ብትገኝና? ሥጋዊ ሕይወቷን ለማሻሻል ብትደክምም በመንፈሳዊ ሕይወቷ በኩል ግን በጣም ደካማ ነበረች ይህም ሊሆን የቻለው ወላጆቿ ገና ከሕፃንነቷ ጀምረው በአምልኮተ ጣኦት ፍቅር ስለአሳደጓት ነው ።

ይሁን እንጂ የኑሮ ጓደኛዋ ያዕቆብ እግዚአብሔር ለሚያምኑት ሁሉ የሚረዳና ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን በየጊዜው ቢገልጥላትም በእግዚ. አብሔር በኩል የነበራት አምልኮት ከሞላ ጎደል ከመሆኑም በቀር አሳብ የቀና አልነበረም ሁለት ልብ ከመሆኗም የተነሣ አንድ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሌላ ጊዜ ደግሞ አባቷ ወደሚያመልከውጣኦትስለምትሳብአድራጐቷም ሆነ እምነቷ በአንድ ዓላማ የጸና አልነበረም ። ሐሳቧም በየጊዜው ይለዋወጥ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያብራራልናል ።

ባለቤቷ ያዕቆብ ከአባቷ ከላባ ጋር ተጣልቶ ጓዙንና ቤተሰቡን ይዞ በኮበለለ ጊዜ የእምነት ግዴታዋን ፈጽማ የረሳችው ራሔል አባቷን ከማስተየሚ ሌላ በእግዚአብሔር ላይ የማይገባ ክፉ ነገር አደረገች ልቧም በሁለት ነገር የተከፈለ ስለነበር ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ በሐሰተኛ ጣዖት ፍቅር ከመመረዟ የተነሣ አባቷ ያመልከው የነበረውን ተራፊም ወይም የጣዖት ምስል ሠርቃ ከባለቤቷ ጋር ኮበለለች ።

አባቷ ላባም የያዕቆብን መኮብለልና ራሔልም ከርሱ ጋር ጠፍታ መሄዷን ስለሰማ ሰባት ቀን ገስግሶ ከመንገድ ደረሰባቸው ያዕቆብንም አምላኮቼን ሰርቀህ ለምን መጣህ? ሲል ጠየቀው ያዕቆብም አምላኮችህን ሰርቆ የመጣ ሰው ቢገኝ እሱ ይሙት የአንተ የሆነው በእኔ ዘንድ የተገኘ እንደሆነ በወንድሞቻችን ፊት ፈልግ አለው ። ይኸውም ራሔል እንደሰረቀችው አያውቅም ነበርና ነው ።

ላባም እንደተነገረው አምላክ እያለ የሚጠራቸ[...]ን ጣዖቶች በየ ድንኳኑ እየገባ ፈ[...]ገ ሊያገኛቸው



www.ethiopianorthodox.org

አልቻለም በመጨረሻም ራሔል ወዳለችበት ድንኳን ገባ አጥብቆ ጠየቃት ራሔልም ነገሩ እንዳይገለጥባት ስለፈራች የሰረቀቻቸውን የአባቷን ጣዖቶች ወስዳ ከግመል ኮርቻ በታች ሸሽጋቻቸው በላያቸውም ላይ ተቀመጠችባቸው አባቷም በድንኳኑ አካባቢ እየተዘዋወረ ፈለገና ስላጣ እየተናደደ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ራሔል ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ከተቀመጠችበት አልተነቃነቀችም ነበር ። ዘፍ.፴፩ ፩-፴፭።

እንግዲህ በራሔል በኩል የተደረገውን የእምነት መላላት የተረዳን ይመስለኛል ። የተመለከትነው ራሔል መልከቀና ብትሆንም እንኳ በምግባርና በእምነት በኩል ግን ቀና ሁና አላገኘናትም አካሄዷ ሁሉ ጣዖት መውደድ ስለነበረ የሥራዋ ውጤት አላማረላትም።

ምክንያቱ ጣዖት ሰውን የመማረክና የማታለል ኃይል ስላለው ነው ስለዚህ እሷን ከሥልጣኑ በታች አድርጐ ሊገዛትና ልቧንም ሊስበው የቻለ አምልኮ ጣዖትም ከኃጢአት ሁሉ የከፋ በመሆኑ መንፈሳዊ ዓይኗን አጨለመባት በልቧም የነበረውን መንፈሳዊ ምግባርና እምነት አጠፋባት ።

ከዚህም የተነሣ የጣዖት ፍቅር አእምሮዋን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ስለ ያዘው የነበራት ርኅራኄ ጨርሶ ጠፍና የጭካኔ ጠባይ አደረባት ከወገኖቿ መለየት ፡ ከሀገሯ መውጣት ሳያሳዝናት ከጣዖቱ ተለይቶ መሄድ ስለቀረቀራት ጣዖቶችን ደብቃ ይዛ ሄደች ። ይህም ሁኔታ በባልዋ በኩል የነበራትን ታማኝነት ሲያቀዘቅዘው በእግዚአብሔርም ዘንድ የነበራትን እምነት ወደ ክህዴት እንደለወጠባት ተግባሯ ይመሰክራል ። ይኸውም አምላክህ አምላኬ እምነትህ እምነቴ አገርህ አገሬ ነው ስትል ያዕቆብን አምና ከተከተለች በኋላ እንደገና ሌላ ሰው ሠራሽ ጣዖት ይዛ ከርሱ ጋር ስለሄደች ነው ።

ምንም እንኳን ያዕቆብ ይህን መሳይ መጥፎ አድራጐትን ባያውቅም በጊዜ ብዛት ነገሩ ስለገባው "እንግዶቹን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ" ንጹሐንም ሁኑ ልባችሁንም ለውጡ ተነሡ ወደቤቴልም እንውጣ በዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ በሄድሁበትም መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው ለእግዚአብሔር መሠዊያ አደርጋለሁ ሲል እሷም ሆነች ይህን መጥፎ ተግባር የሚፈጽሙ ሁሉ ይህንን የመሰለውን መጥፎ ስህተት እንዲያስወግዱ መከራቸው ።

ምክሩን በመስማት ሚስቱና አብረዋት ያሉት ሁሉ በእጃቸው የሚገኙትን የጆሮአቸውን ጉትቻዎች እንግዳ ጣዖቶቻቸውንም ለያዕቆብ ሰጡት እሱም በሴኬም አጠገብ ካለችው ዛፍ በታች ቀበራቸው ዘፍ.፴፭ ፩ ፭ እንደተነገረውም ያዕቆብ ይህንን በመሥራቱ የእምነቱን ጽናት በተግባር አስመሰከረ ። ራሔልም ከነቤተሰቧ ጭምር ጥፋቷን አውቃ ስለኃጢአቷ በመፀፀት ሸሽጋው የነበረውን ጣዖትም ሆነ አምልኮ ጣዖት ትፈጽምባቸው የነበሩትን የጅዋንም የጆሮዋንም ጌጥ አውልቃ ለእግዚአብሔር ሰጠች ።

የያዕቆብን ምክር ሰምታ የእምነቷን ግዴታ አውቃ ወደ እግዚአብሔር በመመለሷ ከራሔል ብዙ ትምህርት ልንወስድ እንችላለን። ራሔልም ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ ሳትመለስ እስከ ሕይወቷ መጨረሻ ድረስ በእግዚአብሔር እንዳመነች ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለየች ስንረዳ ደግሞ ንስሐ መግባት ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን እንረዳለን ።

ዛሬም ቢሆን ይህ ሁኔታ በኅብረተሰባችን መካከል አልፎ አልፎ በአንዳንድ ግለሰብ ዘንድ ሲፈጸም ይታያል በመሆኑም ሚስቱንና ቤተሰቦቹን እየመከረ ከጥፋት የሚመለስ ከመጥፎ ጠባይ አላቆ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅና ትክክለኛ ወደሆነው ማኅበራዊ ኑሮ የሚያቀርብ ካህን ብቻ ሳይሆን እንደያዕቆብ ያለ መልካምየባልረዳትሐዋርያሊኖር ይገባል ። እንዲሁም እንደራሔል የባላቸውን ምክር ተቀብለው ጥፋታቸውን አምነው ከሚሠሩት ነውር ሁሉ የሚመለሱ ሴቶች ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ከአንድ የውሃ ምንጭ መራራና ጣፋጭ ውኃ እንደማይገኝ ሁሉ ባልና ሚስት አንድ አካል ስለሆኑ መራራ ሳይሆኑ ጥሩ ምግባር እና ጥሩ እምነት ሊኖራቸው ይገባል።

ወ/ት መዓዛ አስማማው

# የመጀመሪያው ተአምር

በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ በእግዚአብሔር ኃይል ብዙ ተአምራት እንደተደረጉ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል ። ነገር ግን በገሊላ አውራጃ በቃና መንደር የታየው ተአምር የመጀመሪያ የተባለበት ምክንያት መድኃኒታችን ክርስቶስ ፫ ዓመት ከ፫ወር በዓለም ላይ እያስተማረ ካደረጋቸው ተአምራት መጀመሪያው በመሆኑ ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላሳ ዓመት ሲሞላው በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ወዲያው ወደገዳመ ቆሮንቶስ በመሄድ ፵ ቀን ከጾመ በኋላ በወጣ በሦስተኛው ቀን በሠርግ ቤት ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል ። ወዝንቱ ውእቱ ቀዳሚ ተአምር ዘገብረ እግዚእነ ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ፡የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው የተአምራቱ መጀመሪያ ይህ ነው" ዮሐ. ፪—፲፩ ፡

ይህም የሆነው የካቲት ፳፫ ቀን ሲሆን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የውሃ በዓል ከውሃ በዓል ጋር መከበር አለበት በማለት ፳ኛም ይህ ቀን የሚውለው ብዙ ጊዜ በጾም ውስጥ ስለሆነ ከበዓለ ጥምቀት ቀጥሎ ጥር ፲፪ ቀን እንዲከበር አድርገዋል ።

ስለዚህ በሀገሩና በቦታው ስም ቃና ዘገሊላ በመባሉ በየዓመቱ በዚሁ ቀን ሲከበር ይኖራል ። በዚህ ቀን መድኃኒታችን ክርስቶስ ዶኪማስ በሚባል ሰው ቤት ሠርግ ተጠርቶ ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ጥሪውን በማክበር ተገኝቷል። ሰው እንደመሆኑም ከእድምተኞቹ ጋር አብሮ በመብላትና በመጠጣት ሕገ ሰብእን (ሥርዓተ ሰብእን) ፈጽሞአል ። እንደ አምላክነቱ ደግሞ ንጹሑን ውሃ የወይን ጠጅ አድርጓል ። ይህም መለኮት ከትስብእት ፡ ትስብእት ከመለኮት ጋር ምንጊዜም አለመለየቱን ያስረዳል ።

በሠርግ ቤትም መገኘቱ የጋብቻን ክቡርነት ይገልጻል ። በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ የሁለት ተጋቢዎችን ጋብቻ እንደባረከ በሃይማኖት ጸንተው በምግባር ታንፀው በሕግና በሥጋ ወደሙ ለሚጋቡ ባልና ሚስት ሁሉ ክርስቶስ ከመካከላቸው ተገኝቶ ጋብቻቸውን እንደሚባርክላቸው ለመረዳት ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው ።

ስለዚህ ጋብቻን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ሁሉ በቅድሚያ ክርስቶስን መጥራት ያስፈልጋቸዋል ።

አንድ ሰው ድግሥ ደግሦ ዘመድ አዝማዱን ጠርቶ በሚጋብዝበት ጊዜ ድግሡ አልቆበት የሚያቀርበው ሲያጣ ምን ያህል ሐፍረት እንደሚሰማው ማሰብ አያዳግትም ። በዚህ ሠርግ ቤት የተጠራው ሁሉ ሳይዳረስ የወይን ጠጅ (መጠጡ) ስለአለቀባቸው እመቤታችን ድንግል ማርያም ለተቸገረ ሁሉ አማላጅ እንደመሆኗ ወደልጇ ክርስቶስ ጠጋ ብላ "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም" አለችው ይህም ለሱ ጠፍቶት ሳይሆን ማንም ቢሆን ችግሩን ወደ እግዚአብሔር ማመልከት እንዳለበትና የእመቤታችንንም አማላጅነት ለማጠየቅ ነው ።

ወደ አገልጋዮቹም ሄዳ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው ኢየሱስም ጋኖቹን እስከ አፋቸው ድረስ ውሃ ሙሉአቸው ብሎ አዘዘ አገልጋዮቹም እንደታዘዙት በስድስት ጋኖች ውሃውን ሞሉ ይህም እምነበ አልቦ አምጥቶ የሚሰጥ አምላክ መሆኑ ሲታወቅ ውሃ ቅዱ ፡ ጋኖቹን ሙሉ ማለቱ የድካም ውጤት የሚባርክ እንጂ ሳይሠሩ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ያስረዳል ።

ከዚህም በኋላ ለአሳላፊዎቹ ቅዱና ለአሳዳሪው (ለሠርግ ቤቱ ኃላፊ) ስጡ አላቸው አሳዳሪውም ቀመሰና ከወዴት እንደመጣ ስላላወቀ አደነቀ ሙሽራውንም ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ከሰከሩ በኋላ መናኛውን ይሰጣል ። አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስካሁን አቆይተሃል በማለት ተገረመ ዮሐ. ፪.፫—፲ ፡ ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ከጌታም ሆነ ከእመቤታችን የተሰጣቸውን ትእዛዝ በሚፈጽሙበት ጊዜ ሁኔታውን ስለአዩ ያውቁ ነበር ።

እዚህ ላይ ወይኑ ያለቀው ደጋሾቹ ለእድምተኞቹ በቂ መጠጥ ባለማዘጋጀታቸው ይመስለን ይሆናል ። ይህ የሆነው በነሱ ጉድለት ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥ ዘንድ ነው ለዚህም ምሳሌ ዓይኑን ያበራለት ዕውር በማን ኃጢአት እንደታወረ ደቀ መዛሙርቱ በጠየቁት ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ መለሰ የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም" ይላል ዮሐ. ፱—፫ ፡

ይህች አምላካዊ ተአምር የተገለጠባት የሠርግ ቤት ለቤተ ክርስቲያን ጥሩ ምሳሌ ናት ለሠርጉ ቤት ዋናው ሙሽራው እንደመሆኑ ለቤተ ክርስቲያንም ባለቤቷ ራሱ ክርስቶስ ስለሆነ "መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን (የቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋ) በመባል ይጠራል። ወደ ሠርጉ ቤት የተጠሩ ሁሉ በልተው ጠጥተው ረኀበ ሥጋ ፡ እንደተወገደላቸውና ከጥማቸው ረክተው እንደተደሰቱ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩ ምእመናንም በንስሐ ታድሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ሥጋውን በልተው ደሙን ጠጥተው ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው ዘለዓለማዊ ደስታን ያገኛሉ።

ውሃው ወደ ወይን ጠጅ እንደ መለወጡ በጸሎተ ቅዳሴ ሕብስቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ኤጲፋንያ

## ከብፁዕ አቡነ አብርሃም

ኤጲፋንያ ጥሬ ቃሉ ከግሪክ የተወረሰና የመጣ ቃል ነው ። በግእዝ ቋንቋችንም አስተርእዮ ማለት ሲሆን ግሣዊ መደቡ ግን አስተርአየ "ታየ ተገለጠ ታወቀ ከለው ግሥ የወጣ ንዑስ አንቀጽ ነው ፤ አስተርአየ ታየ ተገለጠ ታወቀ ተብሎ የተነገረለት ማን ነው ቢባል ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ (ዮሐ. ፩ ቁ ፲፰) እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም እንደተባለው ገጸ ባሕርዩ በፍጡር አእምሮ የማይመረመረው የአምላክነቱ ገጽታ ታይቶ የማይታወቀው ፤ ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጊዜው ጊዜ ማለትም የሰውን ዘር ከነበረበት ፍዳ መርገም ጫና የሚያድንበት በክቡር ወርቀ ደሙ የሚዋጅበት ጊዜው ሲደርስ ልዑል ባሕርዩን ዝቅ በማድረግ ትሑት ባሕርያችንና አካላችንን ባሕርዩ አካሉ በማድረግ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ከተጠበቀችው ለእናትነት በልዩ ምርጫ በመንፈስ ቅዱስ ከተመረጠችው ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ተዋህዶ በኛው መጠን ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ስለ ታየ የማይታወቀው አምላክ ታወቀ የማይታየው አምላክ ታዩ ተባለ ።

ከዚህም ጋር ከወልድ በቀር አብን የሚያውቀው አልነበረም ወልድ ሲገለጥለት ለወደደው ይገልጥለታል እንጂ ማቴ.፲፩ ቁ. ፲፯ ያለውን ተግባራዊ ለማድረግ የላከኝ አብም ስለ እኔ መስክሮአል ዮሐ. ፭ቁ.፴፯ እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል ዮሐ.፲፭ ቁ. ፳፮ ብሎ በመጠቆም በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ በቆመ ጊዜ የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ በደመና የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በመታየት ምስክርነታቸውን በመሥጠት ሦስትነታቸውን ስለ ገለጡ ያልታወቁት ታወቁ ተባለ ማቴ. ፫ ቁ. ፲፮—፲፯ ማር. ፩ ቁ. ፲—፲፩ እርሱ ቅሉ ጌታ እኔን ያየ አብን አይቶአል በማለት አረጋግጦልናል ዮሐ. ፲፬ ቁ ፱ ።

ሆኖም በዘመነ አበው ልዩ ልዩ በሆነ አምሳል ታይቶ ነበር ። "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ገጽና ከአባቶችም ላንዱ ለአብርሃም በመምሬ ዛፍ እግዚአብሔር ተገልጾለት" የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬ ጊዜ በውነት ወዳንተ እመለሳለሁ ብሎ ዘፍ ፲፰ ቁ ፲ ፤ ይህን ተስፋ በነገረው (በ፪ሺህ) (በሁለት ሺህ) ዓመት በሥጋ ተገልጦ የሚታየውን መታየት ነግሮታል ። በዘመነ ነቢያትም ከነቢያት አንዱ ልዑለ ቃል የተባለው ኢሳይያስ ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረገርምና ከፍ ባለ ዙፋን ተቀምጦ አየሁት" ብሎ አል ኢሳ. ፮ ቁ. ፩።

እንዲሁ ዳንኤልም "በሌሊት ራእይ አየሁ ፤ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር መጣ ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለው ደረሰ ወደፊቱም አቀረቡት ወገኖችና አሕዛቡ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሠጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው ። መንግሥቱም የማይጠፋ ነው ብሏል (ዳን.፯ ቁ.፲፫) ብልሁ ሰሎሞንም በመኃይል ምሳሌው ሰው ሆነህ ሥጋ ለብሰህ መልክህ ያማረ ነው ፊትህን (መልክህን አሳየን) መዝ.፬.ቁ.፪ ቃልኽ ያማረ ነውና ድምፅህን አሰማኝ መኃ.፪.ቁ ፲፬—ብሎአል ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር መታየት ዓለም አልዳነም ፤ (ወበዝንቱ ኩሉ አስተርእዮ ዘእግዚአብሔር ኢድኅነ ዓለም እንዳለ ሳዊ ህይማ አበው ፹፰ ቁ ፴፫—፴፰ አሕዛብም ከነበሩበተ አምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር አልተመለሱም ። በተለይም በደብረ ሲና በአምሳለ ንጉሥ ተገኝቶ ሕግ የሠራላቸው መመሪያና መተዳደሪያ ትእዛዝ የሠጣቸው አርባ ዘመን በሲና በረሃ ሲጓዙ መና ከደመና እያወረደ ውሃ ከአለት ድንጋይ እያፈለቀ የመገባቸው ወገኖቹ እስራኤል በቀን ደመና ጋርዶ በሌሊት ብሩህ ዐምደ ደመና ተክሎ እያበራ፤ አስደናቂ የሆነ ልዩ ልዩ ታምራት በማድረግ ከባድ ከሆነ የጠላት አገዛዝ ያወጣቸው እግዚአብሔርን ክደው ውለታውንም ሁሉ ረስተው (ፌጎር የሚባል ጣዖት አመለኩ ብሏል) ሳዊ ፹፭ ቁ ፴፭ ።

እንግዲህ ባለፉት ዘመናት ሁሉ በልዩልዩአምሳልየእግዚአብሔር መታዩት ለድኅነተ ዓለም ምንም አልጠቀመም ነበር ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መታየቱና መገለጡ ግን ዓለም በናፍቆትና በጉጉት ለሚጠብቀው ድኅነቱ አፈጻጸምምቹ ሆኖ ተገኝቶአል ምክንያቱም የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ የጠፋውን ሊሻ የተጎዳውን ሊያድን መጥቶአል ማቴ. ፲፰ ቁ. ፲፩ ሉቃ ፲፱ ቁ ፲" እያለ ሲያውጅ እየሰሙ መናፍስት ርኩሳን ሁሉ እየጮሁ ይሸበሩ ነበር ። በሥጋውም በነፍሱም ሠልጥነው ካደሩበት ሰው እንዳያስወጣቸው ቢያስወጣቸውም በሰፊ ሜዳ ላይ ከተሠማሩት የእሪያ መንጋዎች እንዲያድሩ ይለምኑት ነበር ጌታም ርኩሳን መናፍስት ምንጊዜም ጥረታቸው የሰው ዘር የሚጎዳበትን ጥፋት ብቻ መቀየስ መሆኑን ስለሚያውቅ በእሪያዎቹ እንዲያድሩ ወዲያውኑ ፈቀደላቸው ምክንያቱም እባብን ግደል ከነበትሩ ገደል እንደሚባለው ምሳሌ እሪያዎቹ ከገደል ወድቀው ከባሕር ጠልቀው ሲያልቁ ርኩሳን አጋንንትም በዚያው በኩል ወደ ሲኦል ስለሚወርዱ በሠሪውም ሆነ በአሠሪው ትክክለኛ ፍርዱን ለመሥጠት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክም ፍጹም ሰውም ሆኖ ከመታየቱ የተነሣ በልዩ ልዩ ደዌ ተይዘው የሚሠቃዩት በሽተኞች ሁሉ ዓይን ያላቸው ሰብአዊ መልኩን እያዩ አውሬውን ደግሞ በመንገድ ሲያልፍ በየምክንያቱ ፤ እንደየፍላጎቱ የሚከተለውን ሕዝብ አጀታና ግርግርታ በመስማት "የዳዊት ልጅ ጌታ ሆይ" አትለፈን ይቅርታህንና ምሕረትህን ለግሠን እያሉ በማሳዘን ልመና ሲያቀርቡለት ፤ ምን ሊደረግላቸው እንደሚወዱ እየጠየቀ በማያዳግም ቃል የማዳኑን ሥራ ይፈጽምና ያከናውን ነበር ።

እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር (እንደ ሃይማኖታችሁ ይሁን) ያለውን ቃል ነው እርግጥ ያለሃይማኖትእግዚአብሔርን ልናገለግለው አገልግለንም ደስ ልናሰኘው አንችልም እርሱም ፍላጐታችን እያሟላልንም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደእግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንደሚሠጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል ተብሎ አልና ዕብ ፲፩ቁ ፮ ። ስለዚህ በኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ሃይማኖትጸንተን በምግባር በትሩፋት አጊጠን ሁላችንም ወደ መንበረ ፀጋው እንቅረብ ይህንንም ለማድረግ በቸርነቱ ይርዳን ። አሜን ።

---

ወደ ሥጋ መለኮት ወይኑ ወደ ደመ መለኮት ፤ ይለወጣል በሠርግ ቤት ሙሽሮቹ በሆታ በእልልታ እየታጀቡ እነሱን የሚያሞግሥ ሙዚቃና ዘፈን እንደሚሰማ በቤተ ክርስቲያንም መርዓዊ ክርስቶስ በመዘምራኑ በቀሳውስቱና በዲያቆናቱ ባማረ ጣዕመ ዜማ ሲመሰገን ይኖራል ።

ወደ ሠርግ ቤት የሚመጡ (የተጠሩ) የሙሽራው ወገኖች የሆኑ ናቸው ። ወደ ቤተ ክርስቲያንም የሚመጡ የክርስቶስ ወገኖች ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያን ሥጋ ወደሙንና ትምህርተ ወንጌልን ደግሞ ትጋብዛለች ለዚህም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በትምህርተ ወንጌል ጠራችሁ" ፪ኛ ተሰ. ፪—፲፬ ።

አሁንም ክርስቶስን ዘወትር በጸሎት ከጠራነው ቤታችንና ሀብታችንን ይባርክልናል የመረረውንም ኑሮአችንን ያጣፍጥልናል ። ውሃው በተአምር እንደተለወጠ እኛም በንስሐ ተለውጠን መራራ ኃጢአት ተወግዶልን ጣዕመ ዓለምንና ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን እናገኛለን ።

መ/መንክር ዋሴ

---

# የዓፀደ ወይን ምሳሌነት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቅደስ ገብቶ ብዙ ሕዝብን በሚያስተምርበት ጊዜ የካህናት አለቆችና ጸሐፎች ትምህርቱን ለማደናቀፍና ላለመቀበል በተንኮል እየተነሡ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቁት ነበር ። እሱም የልባቸውን ክፋት በመመልከት ጥያቄያቸውን በጥያቄ እየመለሰ ቃሉን ስለአለመቀበላቸውም የተለያዩ ምሳሌዎችን እየመሰለ ይነግራቸው ነበር ከምሳሌዎቹም አንዱ ይህ ነው ።

የወይን አትክልት የተከለ ባለ ቤት ሰው ነበረ ቅጥርም ቀጠረለት መጥመቂያም ማስላት ግምብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ ። የሚያፈራበትም ጊዜ ሲደርስ የወይን ፍሬ ያመጡለት ዘንድ መልእክተኞቹን ላከ ። ገበሬዎቹም መልእክተኞቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት አንዱንም ገደሉት ፤ ሌላውንም ወገሩት ደግሞ ብዙ መልእክተኞችን ላከ እነሱንም እንዲሁ አደረጉዋቸው ። በመጨረሻ ልጁን ላከ እርሱንም እንግደለውና ርስቱን እንውሰድ ተባባሉ ይዘውም ወደ ውጭ አወጡና ገደሉት እንግዲህ የወይኑ ጌታ በመጣ ጊዜ ምን ያደርጋቸዋል ? ሲል ጠየቃቸው ። እነርሱም ክፉዎቹን በክፉ ያጠፋቸዋል ወይኑንም በየጊዜው ፍሬውን ለሚያስረክቡ ገበሬዎች ይሰጣቸዋል በማለት መለሱለት" ማቴ. ፳፩—፴፫—፵፮ ።

ይህ ምንባብ እያንዳንዱ ቃል የተለያዩ ምሳሌአዊ ትምህርቶችን ያዘለ ነው ። የዓአፀደ ወይኑ



www.ethiopianorthodox.org

ባለቤት ወይኑን ተክሎ ፣ አጥሩን አጥሮ ፣ ለወይኑና ለገበሬዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟልቶ መሄዱ ትእዛዙን ተቀብለው ሥርዓቱን አክብረው እንዲኖሩ ሕግ መሥራቱን የሚያስረዳ ነው ።

ወይኑም የሚያፈራበት ጊዜ ሲደርስ መልእክተኞቹን ወደገበሬዎቹ መላኩና እንዳልተቀበሉዋቸው ሃይማኖት የሚይዙበት ፣ ምግባር የሚሠሩበት ጊዜ ሲደርስ ሕገ እግዚአብሔርን የሚያስተምሩ ፣ ትንቢት የሚናገሩ ታላላቅ (ዓበይት) ነቢያትን ቢልክላቸው እኩሎቹን ደብድበው ፣ እኩሎቹን ገድለው ሌሎቹን በድንጋይ ወግረው አስቃይተዋቸዋል ።

እንደሁለተኞቹም መልክተኞች ታናናሽ (ደቂቅ) ነቢያትን ከበፊተኞቹ አብዝተው እንዲያስተምሩ ባስነሳ ጊዜ እነሱንም እንዲሁ አድርገዋቸዋል ።

3ኛ/ ልጄንስ ያፍሩታል ፣ ያከብሩታል ብሎ ልጁን ቢልክ እሱንም ይዘው ወራሹ ይህ ነው ኑ እንግደለውና ርስቱን እንውሰድ በመባባል ወደውጭ አውጥተው እንደገደሉት እግዚአብሔር አንድ ልጁን በሥጋ ወደዚህ ዓለም በላከው ጊዜ ትምሕርቱንና ታምራቱን ያዩ ፣ ብዙ ሕዝብ ስላመኑበትና ስለተከተሉት ጸሐፍት ፈሪሳውያን ያለእኛ አዋቂና መምህር የለም በማለት በቅንአትና በምቀኝነት ተነሡበት በእርሱ ማመንና ትምህርቱን መቀበል ክብራቸውን የሚቀንስ ፣ ሙያቸውን የሚያሳንስ መስሎ ስለታያቸው አሥረው ገርፈው ወደቀራንዮ አውጥተው በስቅላት እንዲሞት የማድረጋቸው ምሳሌ ነው ።

በመጨረሻም የወይኑ ጌታ ሲመጣ ምን ያደርጋቸዋል ? ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ምሳሌው በነሱ የተነገረ መሆኑ የገባቸውና የተረዱት ይህን የሚያደርግ የለም ፣ በማለት ክደዋል ። ያልገባቸው ደግሞ እነዚህን አጥፍቶ የወይኑን ፍሬ በጊዜው ለሚሰጡ ገበሬዎች ይሰጣል በማለት እውነቱን መልሰዋል ።

ይህም ሕግ የሠራላቸው ሥርዓት ፣ ያቆመባቸው እነሱ ፣ ስለካዱትና ስላልተቀበሉት እነሱን አጥፍቶ በእነሱ ፋንታ ላመኑትና ለተመረጡት ገነት ፣ መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርሳቸው መሆኑን ያስረዳል (ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ ፣ እርሱም ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው ። እሥራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም" ሮሜ ፲፩—፴፩ ።

በሌላም ምሳሌ አፀደ ወይን የወይን ቦታ ሲሆን ባለቤቱ ራሱ ነው እንደወይኑ ቦታ ቤተ መቅደስን አቁሞ ሕገ ኦሪት እንዲነገርባት ነቢያት ካህናትን ሠርቷል ። ኋላም በዘመነ ሐዲስ ቤተ ክርስቲያን አቋቁሞ ወንጌል እንዲሰበክባት ፣ ሥርዓተ ጥምቀት እንዲፈጸምባት ፣ ሥጋ ወደሙ እንዲፈተትባት አድርጓል ። በውስጧም ሕገ መንጌልና ሕገ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ሐዋርያትና ሊቃውንት ስለ እርሱ ሲያስተምሩ ፣ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ ፣ በአላውያን እጅ ሕይወታቸውን ያሳለፉ ብዙዎች መሆናቸውን ያስረዳል ።

መድኃኒታችን ክርስቶስ ይህንን ምሳሌ ያመጣው ጸሐፍት ፈሪሳውያን በሚያውቁት እንዲረዱት ለማድረግ ሐሳቡን ከኢሳ ፭—፩፡፪፣ በመጥቀስ ነው ። ቃሉም "ለወዳጄ በፍሬያማው ኮረብታ ላይ የወይን ቦታ ነበረው ። በዙሪያው ቆፈረ ፣ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ ምርጥ የሆነ ሐረግ ተከለበት በመካከሉም ግምብ ሠራ ደግሞም የመጥመቂያ ጉድጓድ ማሰለት ወይኑም ያፈራ ዘንድ ተማመነ ዳሩ ግን ኮምጣጤ ፍሬ አፈራ" ይላል።

ይህም ወይን የተባሉ እሥራኤል መሆናቸውን ያረጋግጣል እሥራኤል በረሐብ ምክንያት ወደ ግብፅ ወርደው በባእድ አገር ግዛት ስለ ጠናባቸው ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ባደረገ ጊዜ ውሃ ከድንጋይ እያፈለቀ ፣ መና ከሰማይ እያወረደ ፣ ሌሊት በብርሃን ቀን በደመና እየመራ ሲረዳቸው የነበሩ ሕዝብ ፣ እርሱን ትተው ጣዖት አመለኩ ፣ ሕጉንም ረሱ ። እርሱንም በደሉ ፣ ስለዚህ ግብራቸው እንደሬት ስለመረረውና እንደኮምጣጤም ስለኮመጠጠው በቁ ፫/ ላይ ፱ እናንተ በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የይሁዳ ሰዎች ሆይ በኔና በወይኔ ቦታ መካከል እስቲ ፍረዱ እያለ ያማርራቸዋል ። ቅዱስ ዳዊትም ዓፀደ ወይን የተባሉ እሥራኤል መሆናቸውን ሲገልጽ አፀደ ወይን አፍለሰከ እምግብፅ (እስራኤንን ከግብፅ አወጣህ ይላል) መዝ ፸፱—፰ ።

እመቤታችን ድንግል ማርያምንም አፀደ ወይን ሐረገ ወይን ፣ ይላታል ። የዓለም መድኃኒት የሆነ ፍሬ ሕይወት ክርስቶስን አፍርታ ተገኝታለችና እንዲሁም የእመቤታችን ትውልዷ ከእሥራኤል ወገን እንደመሆኑ ዳዊት የተናገረው (እሥራኤልን ከግብፅ አወጣ) ትንቢታዊ ቃል ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በግብፅ ተሰዳ ቆይታ መመለሷን ያስረዳል።

ይህ የአፀደ ወይን ምሳሌነት አማኞች ለሆንን ሁሉ ይመለከታልና ለወይኑ አስፈላጊውን ሁሉ እንዳዘጋጀለት ለእኛም ሕገ ወንጌልንና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ከነመምህራኖቿ አሟልቶ ሰጥቶናል ። ታዲያ እምነታችንን አጽንተን ትእዛዙን አክብረን በመገኘት የጌታችንን መምጣት የምንጠባበቅ ነን ወይ ? በማለት ራሳችንን መጠየቅ አለብን ።

የመንፈስ ፍሬ የተባሉ ፍቅርን፡ ደስታን ፣ ሰላምን ፣ ትእግሥትን ፣ ቸርነትን ፣ በጎነትን ፣ እምነትን ፣ የዋህነትን ፣ ራስ መግዛትን አፍርተን እንድንገኝ ጌታችን ይጠብቅብናል ገ.፭፣፳፪—፳፫። ፍሬቢስ ሆነን ከተገኘን ግን መድኃኒታችን ክርስቶስ ፍሬዋን" ፈልጐ ባጣባት ጊዜ እንደረገማት በለስ መሆን ነው ። " በመንገድ አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርሷ መጣ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና ለዘለዓለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት በለሲቱም ያንጊዜውን ደረቀች ። (ማቴ. ፳፩—፲፱ ይህች በለስ አፍርታ ብትገኝ ኖሮ ከክርስቶስ ምን ያህል በረከት አግኝታ ለዘለዓለም ለምልማ መኖር ትችል እንደነበር ከትምህርቱ መረዳት አያዳግትም።

እንግዲህ በለስ ወይም ወይን የተባልን ምእመናን ሁሉ መሆናችንን ተረድተን ፣ ጽድቅን አፍርተን ከከፋት ርቀን የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ተግተን መጠባበቅ ይገባናል ።

መ/መንክር ዋሴ

# ወንድምህን እንደራስህ ውደድ

በዚህች ምድር ላይ በሚገኙ የሰው ልጆች መካከል ያለው ማህበራዊ ግንኙነት መሠረት እንዲኖረው የሚአደርጉና ለሰው ልጅ ህልውና መርህ የሚሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡ አያሌ ጠቃሚ ትምህርቶችና ምክሮች አሉ ።

በመንፈስ ቅዱስ አለባዊነት የተመዘገቡት ቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲተዛዘኑና አንዱ ለሌላው እንዲያስብ ፣ እንዲሁም የእያንዳንዱ ሥነ ልቡናዊ አመለካከት ግላዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው ይመክራሉ ያስተምራሉ።

ለዚህም መሠረት አድርገን የምንወስደው በአሪት ዘሌዋ· ፲፱·ቁ· ፲፯ ላይ "ወንድምህን በልብህ አትጥላው በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥፀው አትበቀል በሕዝብ ልጆች ቂም አትያዝ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ..." የሚለውን መሠረታዊ ትዕዛዝ ነው ይህን ቃል እያንዳንዳችን በዐይነ ሕሊናችን ስንመለከት የማንኛውም የሰው ልጅ የሕልውና ሂደት ከሰዎች ጋር ተስማምቶና ተግባብቶ ፣ ለራሱ የሚአስበውን ያህል ለሌሎችም ማሰብ እንደሚገባ ያስገነዝባል ።

ይህ ከአሥሩ ሕጎች አንዱ የሆነው "ወንድምህን እንደራስህ ውደድ" የሚለው አምላካዊ ትዕዛዝ ለሌሎች ሕጎችም መሠረትና ጉልላት ነው ለምሳሌ አባትህንና እናትህን አክብር አትግደል አታመንዝር አትስረቅ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር…ተብለው ከዚህ ሕግ ጋር የተመዘገቡትን ሕጎች ስንመለከት እነዚህ ሁሉ ሊፈጸሙ የሚችሉት ።

፩ኛ/ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ

፪ኛ/ ወንድምህን እንደራስህ ውደድ በሚሉ ትእዛዛት እንደሚጠቃለሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅ/ወንጌሉ አስረድቶናል ። (ማቴ ፳፪፡፴፯ ።"

ስለዚህም ነው እግዚአብሔር አምላክ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ይመላለስ በነበረ ጊዜ አንድ ሕግ አዋቂ "ከሕግ ሁሉ ማንኛይቱ ትበልጣለች" ብሎ በጠየቀው ጊዜ "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ልብህ ውደድ ፊተኛይቱና ታላቂቱ ሕግ ይህች ናት ፪ተኛይቱ ደግሞ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት በእነዚህ በሁለቱ ሕግም ነቢያትም ተጠቃለዋል ። ሲል የተናገረው ።

የወንጌል መልዕክተኞች ሐዋርያትም ቃለ ወንጌልን በዓለም ዙሪያ ሲአደርሱ ሰዎች እርስ በእርሳቸው መከባበርና መፈቃቀር እንዳለባቸው አስተምረዋል ከሐዋርያት አንዱ ወንጌላዊ ዮሐንስ ዋርያት አንዱ ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለዚሁ ሲገልጽ "እስከ ከመዝአፍቀሮ ወልዶ ዋህደ (ጌታ እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁ ወዶታልና አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ) ይላል ይህን ቅዱስ ዮሐንስ የመዘገበውን ወንጌላዊ ቃል ስንመለከት ቀደም ሲል "ወንድምህን እንደ ራስህ ውደድ ብሎ





www.ethiopianorthodox.org

ትዕዛዝ የሰጠ እግዚአብሔር አም ላክ እርሱም የሰውን ልጅ በመውደዱ በኋለኛው ዘመን የሚወደውን አንድ ልጁን ለዓለም ቤዛ አድርጎ እንደ ሰጠ እንገነዘባለን።

በሌላም በኩል ሐዋርያው ዮሐንስ በ፩ኛ መልዕክቱ በምዕ·፬ ቁ· ፲፱–፳፩ ባለው ላይ ሰዎች እርስ በእርሳቸው መዋደድና መፈቃቀር እንዳለባቸው ሲገልጽ "ወእመሰ ቦ ዘይብል አፈቅሮ ለእግዚአብሔር ወይፀልዕ ቤጾ ሐሳዊ ውእቱ" ማንም ሰው እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ቢኖር ሐሰተኛ ነው· ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያለውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወድ ይችላል እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትዕዛዝ ከእርሱ አለች በማለት ሐዋርያው ዮሐንስ ጽፎአል ።

ከብሉይ ኪዳን ዘምን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ወንድምህን እንደራስህ ውደድ ተብሎ የተሰጠውን አምላካዊ ትዕዛዝ ሰዎች በሚገባ እንዲፈጽሙት ተብሎ በየጊዜው በተነሱ ሊቃውንት ይነገራል ይሁን እንጂ ይህ አምላካዊ ሕግ በመዘንጋቱ ምክንያት በአሁኑ ጊዜያችንም ከላይ እንደተገለጸው በዚህች ምድር ላይ በሚገኙ የሰው ዘሮች መካከል ከፍቅር ማነስ የተነሣ ጥላቻ እየበዛ በመሄዱ የእርስ በእርስ መግባባት የላላ ሁኖ ይታያል ።

እንግዲህ "ፍቅርስ ይደመስሶን ለኩሉን ኃጣውዕ" ፍቅር በደሎችን ሁሉ ያጠፋል ተብሎ እንደ ተጻፈ እያንዳንዳችን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በአጠቃላይም መላውን የሰው ዘር ከልብ በመውደድና በማክበር የመልካም ሥነ ምግባር አበጋዞች ልንሆን ይገባናል በአጠቃላይ ለአንተ ሊደረግልህ የምትፈልገውን መልካም ነገር ሁሉ አንተም እንዲሁ ለወንድምህ አድርግ የሚለውን ክርስቲያናዊ ዓላማ ተግባራዊ እንድናደርግ በቅዱስ መጽሐፍ ክርስቲያን የሆን ሁሉ ታዝዘናል ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# በደምቢዶሎ ያለችው ቤተ ክርስቲያንና ልማትዋ

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለአባሎችዋ የምታስተላልፈው ትምህርትና ለተከታዮችዋ የምትሰጠው ምክር መንፈሳዊውን ትምህርት ብቻ ሳይሆን በዚሁ በምድራዊው ዓለ ምም የሚተዳደሩበትንና በልማት፤ የሚጠቀሙበትን ጭምር ከዚህ በፊት ስታስተምር ኑራለች ዛሬም ሥራዋንና ማስተማርዋን ፈትዛንታ በማስተማር ላይ እንዳለች ሁሉ የሚያውቀው ነው ።

በዚህም መሠረት ላምን ጠብቆ ወተቱን የማይጠጣ አትክልቱን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው ሲል ሐዋርያ ቅዱስ ጳዎሎስ የሰጠውን ሐዋርያዊ ትምህርት በመከተል እንሆ በየአህጉረ ስብከቱና በየአብያተ ክርስቲያናት የልማት ዘርፎች እየተካሄዱ ናቸው ። በዛሬው ጽሑፋችን ልንገልጸው የፈለግነው ግን በደምቢዶሎ ስላለው ልማት ይሆናል ።

ደምቢዶሎ የሚገኘው በወለጋ ሀገረ ስብከት በቄለም አውራጃ ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ፮፻፶ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ የሚገኝ ከተማ ሲሆን በዚሁ አውራጃ ውስጥ ፴፪ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ከእነዚህ ፴፪ አብያተ ክርስቲያናትም መካከል ሁለት በደምቢዶሎ ከተማ የሚገኙ ናቸው እነዚህም ፩ኛው የደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ሁለተኛውም የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነው ።

በዚሁ በቄለም አውራጃና በደምቢዶሎ ከተማ ቀደም ሲል ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በነበሩበት ዘመን በመጠኑ አብያተ ትምህርትና በመንበረ ጵጵስናውም አካባቢ የማንጎ የቡና እና የቡርቱካን የመሳሰሉት የፍራፍሬዎች አትክልት ለምተውበት ቢኖሩም ከዚያ ወዲህ ግን ከልማት ቦታ ሌሎች ድርጅቶች እየተቀራመቱት ቆይቷል ።

ባሁኑ ጊዜ በዚሁ አውራጃ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት እያንዳንዳቸው በየአካባቢያቸው የተለያዩ ልማቶችን እያካሄዱ ናቸው ።

በተለይ በደምቢዶሎ ከተማ በሚገኘው በደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ዓይንን የሚማርኩ ልማቶች እየተካሄዱ ናቸው ይኸውም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ፩ኛ ፪ሺ፯፻ ቡና ተተክሎና ጸድቆ በመልካም ሁኔታ ይገኛል ። ፪ኛ የ፰ ጥማድ በሬ በቆሎና የ፫ ጥማድ በሬ ገብስ ተዘርቶ በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን በዓይናችን ተመልክተነዋል ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

ይቀጥላል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስ[illegible] ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለ[illegible] ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ·
የመልእክት ሣ·ቍ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org